# ክፍል ሁለት

## አመራርና አገልጋይ መሪነት

# ምዕራፍ ሦስት

## በአመራር ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ እይታ፡-

- *"በእስራኤል ውስጥ መሪዎች ስለ መሩ፥ ሕዝቡም ነፍሳቸውን በፈቃዳቸው ሰሰ ጡ፤ እግዚአብሔርን አመስግኑ።" (መጽሐፈ መሳፍንት 5፡ 2)*
- *"እስራኤልም የሚገባውን ያደርግ ዘንድ ዘመኑን የሚያውቁ ጥበበኞች የይሳኮር ልጆች ..." (1ዜና መዋዕል 12፥ 32)*

ባለፈው ምዕተ ዓመትና በያዝነው ምዕተ ዓመት (ሃያኛውና ሃያ አንደኛው ምዕተ ዓመታት) በዓለም ሁሉ ዙሪያ የሚያስደንቅና ከመረዳት በላይ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ እድሳትና እንቅስቃሴ በማያቋርጥ መልኩ እየተካሔደ እንዳለ የዓይን ምሥክሮች ነን።[41] በአንፃሩ ደግሞ ካሪዝማ፥ ካሪዝማቲካና ካሪዝማታ የሚሉት ሐሳቦች ኩላቸው የሥነ መለኮት ትርጉም በላይ ተለጥጠው ስናይና አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች "የግል ፍላጎት መጠቀሚያ" ለማድረግ ሲሞክሩ ስናይ እጅግ የሚያሳስብ እንደሆነ ለመገንዘብ አያዳግትም። አንዳንድ መሪዎችና አገልጋዮች እነ ዚህን ሐሳቦች ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር አመጣጣቸውን ብዙ ሳያስተውሉ እንዲሁ ስለሚጠቀሙባቸው በእነርሱ አመራር ሥር ያለው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ግራ እንዲጋባና  በአመራሩ ላይ የነበረውን እምነት እንዲያጣ ያደርገዋል። ስለዚህም ኩብሉይና ከአዲስ ኪዳን የተወሰነ ባሕርያትን አንስተን ከአመራራቸው የምናስተውላቸው ቁልፍ ሐሳቦች ማየታችን አስፈላጊ ነው ብዬ አምናለሁ።

---

[41] በዚህ ጉዳይ የበለጠ ጥናት ለማድረግ የሚከተሉትን ማንበብ ይቻላል፡- S. M. Burgess and G. McGee, eds., *"The Pentecostal and Charismatic Movements," in Dictionary of Pentecostal and Charistmatic Movements*, (Grand Rapids, MI: Zondervan Publishing House, 1988), 1-6; Peter Hochen, *"The Charismatic Movement," in the Dictionary of Petntecostal and Charistmatic Movements,* 130-160. See also two recent issues of Pneuma: vol. 16, no. 2 (1994) and vol. 18, no. 1 (1996).

## I. አመራር:- የብሉይ ኪዳን እይታ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች መኖራቸው ብቻ ሳይሆን፣ በአመራራቸውም ሞዴል የነበሩ እንዳሉ የታወቀ ነው:: ለምሳሌ:- አብርሃም፣ ሙሴ፣ ኢያሱ፣ ዳዊት፣ ኤልያስ፣ ኤልሳዕ፣ ዘሩባቤል፣ ነህምያና ዕዝራን መጥቀስ ይቻላል:: ሁሉንም የእግዚአብሔር ሰዎች ለማየት ከጊዜና ከቦታ ጥበት የተነሣ ባንችልም፥ የሙሴንና የነህምያን አመራር በመጠኑ ለመዳሰስ እንሞክራለን::

### ሀ. አመራር:- በሙሴ ሕይወትና መሪነት የተገለጸው

የሙሴ የአመራር ስጦታ የተገለጸው በግብፅ ቤተ መንግሥት የፈረዖን የልጅ ልጅ ስለሆነ በአገሪቱ ምሁራን ከተባሉት መካከል መቆጠሩ ብቻ ሳይሆን፣ ለአርባ ዓመታት በእግዚአብሔር ሀልውና ሥር የበጎች እረኛ በመሆን ያገኘው የባሕርይ ለውጥና፥ ሌሎች አርባ ዓመታት ደግሞ የእስራኤል ሕዝብ መሪ ሆኖ በመራቸው ዓመታት ውስጥ ነው:: (የሐዋ. ሥራ 7:22-23፣ 30፣ 42፣ ዕብ. 11:23-29) ሙሴ ምንም እንኳን በተደጋጋሚ ጊዜያት የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን ባለመታዘዛቸው ምክኒያት የሙሴን አመራር ሲጋፉ፥ የራሱ ቤተሰብ የነበሩትም አሮንና ማርያም በቅንዓት ምክኒያት ሲያጣጥሉትም እንመለከታለን:: (ዘኁ 14:4 10 16:41፣ ዘፀ. 32:1-26፣ ዘኁ 12:1-15) እግዚአብሔር ግን ስለ ሙሴ ሲናገር:- "<u>ሙሴም በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሑት ሰው ነበረ</u>" ይላል:: (ዘኁ. 12:3) ከዚህም በላይ ሙሴ በአመራር ችሎታው አፍ የሚያስይዝ ራዕይ ያለውና ፕላን በማድረግ የሚደነቅ እንደ ነበረ በብዙ መልክ ልንመለከት እንችላለን:: (ዘፀ. 18:13-23፣ ዘዳግም 1-3)

የአሪት ዘዳግም የመጀመሪያው ምዕራፍ ሙሴ በእግዚአብሔር ቃል የነጠረ ስለነበረ የራሱን ውሱንነት የሚያስተውል፣ እግዚአብሔር በታማኝነቱ የማይለወጥ እንደ ሆነ አጥብቆ የተረዳና፥ የእስራኤልን ሕዝብ ለመምራት ራሱን በመስዋዕትነት የሰጠ ነበር:: የነበረውንም የአመራር ኃላፊነት ከሌሎች ጋር ለመካፈልና ለመወከል ልዩ ማስተዋልና ጥበብ የነበረው መሪ እንደሆነ አሳይቷል:: (ዘፀ. 18:13-16):: ሙሴን ለዚህ የላቀ የአመራር ደረጃ ሊያደርሱት ከቻሉ ምክኒያቶች አንዱ እየታየ የማይታይ መሪ (visible-Invisible leader) በመሆኑና የአማቹ የዮቶር የማያቋርጥ ምክርን

መስማቱ ነው:: (ዘፀ. 18:1-12) ከዚህም በላይ የማይመጠን ኃይልና ችሎት ያለው እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንዳለ ማወቁም ጭምር ነው:: (ዘዳግም 1:31፤ 33:25-27)

የሙሴ አመራር የላቀና የነጠረ ለመሆኑ ሌላው የተገለጠበት አገላለጥ የነበረውን ራዕይ ለመፈጸም የሚችለው ሌሎች መሪዎችም በማካተትና አብረውት እንዲሠሩ መፍቀድ ብቻ እንደሆነ ማመኑና በሥራ መተርጐሙ ነው:: <u>አንደኛ</u> በመሪዎች መካከል የነበሩት ስጦታዎችና ችሎታዎች ለይቶ መረዳቱ ነው:: "ከእናንተ ከየነገዳቹ ጥበበኞች፤ አስተዋዮችም፤ አዋቂዎችም የሆኑትን ሰዎች ምረጡ:: (ዘዳግም 1:13) <u>ሁለተኛ</u> የተመረጡትንም መሪዎች እንደየ ስጦታቸው በየነገዱ ማሠማራቱ ነው:: የወታደራዊ አለቆችን፤ የንግድ መሪዎችንና የህግ አማካሪዎችን (ዘዳግም 1:15):: <u>ሦስተኛው</u> ሙሴ ትልቁን ስዕል ማየት ያለበትን ያህል በሕዝቡ መሀል ያሉትን ትንንሽ ጉዳዮችም መታሰብ እንዳለባቸው ያምን ነበር:: በአመራር ላይ ያስቀመጣቸውን መሪዎች ልዩ ትኩረት እንዲሰጡ ማድረጉ፤ ጫካውን ለማየት የሚችለውን ያህል÷ ለእያንዳንዱም ዛፍ የሚገደው መሪ መሆኑን ያሳያል:: (ዘዳግም 1:16-17)

ሙሴ የነበረውን የአመራር ችሎታ የገለጸው መደረግ ባለባቸው አስፈላጊ ጉዳዮች ላይ ማተኮሩ ብቻ ሳይሆን፤ በአመራር ላይ ተግዳሮቶች በሚያመጡና ፈታኝ ጉዳዮችም ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠቱ ነው:: እነዚህም አድልዎ፤ ፍርሃትና ብቸኝነት (ዘዳ. 1:16-18) ናቸው:: <u>አንደኛ</u> አድልዎ በጥብቅ የተከለከለ ነው:: መሪዎቹ በድሀና በሀብታም ወይንም ባለጠጋ መሀል ልዩነት ሊፈጥሩ አልፈለገም:: በቤተሰብ መካከል "በሰውና በወንድሙ" ወይም በነገድ መካከል "*ከእርሱም ጋር ባለው መጻተኛ መካከል፤ ወይንም በሕብረተ ሰቡ ባላቸው ቦታ ታላቁን እንደምትሰሙ ታናሹንም እንዲሁ ስሙ*" "*በፍርድ አድልዎ አታድርጉ*" ይላቸዋል:: (ዘዳግም 1:16-17) <u>ሁለተኛ</u> ደግሞ "የሰውን ፊት አይተው እንዳይፈሩም" ያስጠነቅቃቸዋል:: (ዘዳግም 1:17)

## ለ. አመራር÷ በነህምያ ሕይወትና መሪነት የተገለጸው

በመጽሐፈ ነህምያ ላይ የነህምያን አመራር በምናይበት ጊዜ በብዙ ጉስቁልና ውስጥ ተቀምጦ የነበረውን ከምርኮ የተመለሰውን የይሁዳን ሕዝብ የስብዕና ክብር መመለስ፤ ሕይወታቸውም እንዲታደስ በማድረግ፤ እና የፈረሰውን የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንዴት እንዳደሰ ልንገነዘብ እንችላለን:: ነህምያ እንደ መሪ የራዕይ ምንጮች

ከሁለት አቅጣጫ እንደሆነ አስተውሏል፡- ሰብአዊ መነካትና መለኰታዊ መነካት፡፡ ሰብአዊ መነካት (HUMAN TOUCH) የሕዝቡን ሁኔታ ከመጠየቅ፣ መንፈሳዊ ዓይን ከፍቶ ሕዝቡ ያለበትን ጉስቁልና ከመገንዘብ፣ ወደ ውስጥ እስኪሰርፅና አጥንትን እስ ኪሰረስር ድረስ ጊዜ ከመውሰድ ይመጣል፡፡ ነህምያ የሚያገለግለው ሕዝብ ጉስቁልና በቂ መረዳትና የሕዝቡም ሸክም ሳይኖረው ራዕይ ሊኖረው እንደማይችል በጥልቀት ያስተዋለ ይመስላል፡፡ (ነህምያ 1:1-3)፡፡ "መከራ---ስድብ---ቅጠር መፍረስ---በሮች መቃጠል" የሚሉትን ሐሳቦች ስናይ የሐሳብ ዕድገት እንዳላቸው ልንገነዘብ እንችላለን፡፡ ከዚህም በላይ የሕዝቡ ችግር ሥጋዊ ብቻ ሳይሆን፣ መንፈሳዊም ስለነበረና የሕዝቡ መንፈሳዊ ሕይወት መበላሸት ለኢየሩሳሌም ቅጥር መፍረስ ምክኒያት እንደሆነ ስላስተዋለ ካህኑ ዕዝራ አብሮት በአመራር እንዲሰለፍ ሲያደረው እንመለከታለን፡፡

ሁለተኛው የራዕይ ምንጭ መለኰታዊ መነካት (DIVINE TOUCH) ነው፡፡ ነህምያ የእግዚአብሔርን እጅ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ፊት ፈላጊ ነበር፡፡ የእግዚአብሔርን እጅ የሚፈልጉ ሰዎች እጅግ ብዙዎች ናቸው፡፡ በአንፃሩም የእግዚአብሔርን ፊት የሚፈልጉ ግን በጣም ጥቂቶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ ንጉሥ ዳዊት በመዝሙር 27፡ 4፣8 ላይ "*እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመንኩት እርስዋንም እሻለሁ... አንተ ፊቴን እሹት ባልክ ጊዜ አቤቱ ፊትህን እሻለሁ ልቤ አንተን አለ፡፡*" እንዳለው ነው፡፡ (ሉቃስ 10:41-42፣ ፊልጵስዩስ 3:13) ስለዚህም ነህምያ የሕዝቡን ሁኔታ በሰማ ጊዜ ያደረጋቸው አራት ነገሮች እንደነበሩ ልናስተውል እንችላለን፡፡ (ነህምያ 1፡ 4)

- "ተቀምጬ" (Contemplation) ፥
- "አለቀስኩ...አያሌ ቀንም አዝን ነበር" (Compassion) ፥
- "እጾም" (Concentration) ፥
- "እጸልይ ነበር" (Consecration) ፡፡

"አያሌ ቀንም አዝን ነበር" የሚለው ሐሳብ የሚያሳየው የአይሁድ ካላንደር ከካሴሉ ወር (1:1) እስከ ኒሳር ወር (2:1) ድረስ የነበሩትን አራት ወራት ነው፡፡

ከዚህም ሌላ በጣም ልብ የሚነካው ደግሞ የነህምያን ጸሎት ይዘት ስናይ ነህምያ ምን ያህል የጠለቀ የጸሎት ዓለም ውስጥ እንደነበርና በአጭር ጸሎትም ይሁን፥ (2:4፣ 4:4፣ 5:19፣ 6:9፣ 6:14 )፣ ወይንም በረዥም ጸሎት (1:5-11፣9:1-38) የሚያምን እንደ ነበረ ልናስተውል እንችላለን፡፡ የነህምያ ጸሎት፡-

- የእግዚአብሔርን ባሕርይ በመረዳት (1:5)

◆ የሕዝቡን ሁኔታ በማጤን (1፡6-7) ፥

◆ የእግዚአቤሔርን ቃል ኪዳን በማሰብ (1፡8-9) ፥

◆ ራሱንም ከሕዝቡ ጋር በማመሳሰል(1፡6-7) ::

<u>ስለዚህ መሪዎች ራዕይ እንዲያገኙ ካስፈለገ በአንድ በኩል ሰብአዊ መነካት፣ በሌላ በኩል ደግሞ መለኮታዊ መነካት በጣምራ ሊኖሩአቸው ይገባል::</u>

በመጀመሪያ ደረጃ ነህምያ እግዚአብሔር የሰጠውን በግሉ በምስጢር እንደያዘው እናያለን:: (2: 11-16) ያደረገበት ምክኒያትም:-

1) በጆሮው የሰማውን በራሱ ዓይን ለማየት፥ ለማመሳከርና ጥናት ለማድረግ ጊዜ መውሰድ ነበረበት::
2) ራዕዩን ወደ ውስጥ ለማስርጽ (internalize ለማድረግ)፣
3) የራዕዩን አድማስ (Scope) ለማስተዋል፣
4) ራዕዩ የሚያስከፍለውን ዋጋ ለመተመንም፣ በግሉ ጊዜ መውሰድ ነበረበት::

በሁለተኛ ደረጃ ነህምያ ከእግዚአብሔር የተቀበለው ራዕይ የግል ንብረቱ እንዳልሆነና ለእርከን መወጣጫ ሊያደርገው እንደማይገባ ስለተረዳ በቅድሚያ በዘመኑ ለነበሩ መሪዎች፣ ከዚያም ለሕዝቡ ራዕዩን እንዳካፈላቸው እናያለን:: (2: 17-20)

<u>*በሌሎች መሪዎች ሥር መቀመጥ የማይፈልግ መሪ ለአመራርም አይበቃም!!!*</u>

(ሉቃስ 7፡7-9፣ ቆላ. 1፡25፣ 1ቆሮ. 14፡3፣27)

ነህምያ የአመራር ስጦታውንና ችሎታውን የገለጸው በምዕራፍ ሦስት ላይ እንደምናየው ብዙዎች የራዕዩ ተጠቃሚዎች ብቻ ሳይሆን፣ ተካፋዮች እንዲሆኑ በማስተባበር የቡድን ሥራ ሲሠራ በምናይበት ጊዜ ነው::

◆ መሪዎች ለዚህ ራዕይ ልባቸውን ሲሰጡ እናያቸዋለን (3: 1-2፣28...) ካለ ጥቂቶቹ በስተቀር (3፡3፣ 4፣6 )::

◆ ይህ ራዕይ እያንዳንዱን ቤተሰብ እንዲያካትት የተደረገ ራዕይ ነበር:: (3፡3፣ 4፣6 ፣...)

◆ ነህምያ እግዚአብሔር የሰጠው ራዕይ ሁሉንም የሚያካትት (inclusive) እንደሆነ እንጂ፣ በጣም ጠባብና ለይሁዳ አውራጃ ሕዝብ ብቻ (exclusive) እንዲሆን አላደረገውም:: ለምሳሌ የኢያሪኮ ሰዎችን (3፡2፣ የገባዖን ሰዎችን (3፡7)፣ እና የምዕጳ ሰዎችን (3፣7፣15) ወደ ራዕዩ ሲጋበዝ እንመለከታለን::

◆ ይህ ራዕይ የተለያየ ልምድ፣ ችሎታና እውቀት ያስተባበረና የተጠቀመ ራዕይ ነው:: ለምሳሌ:- ካህናትን (3፡1,32)፣ ወርቅ አንጠረኞችን (3፡8)፣ ሽቱ ቀማሚዎ

ችን (3:8) ገዢዎችን (3:9) አለቆችን (3:12)፣ እና ነጋዴዎችን (3:32) ያካተተ ነበር።

ከእግዚአብሔር የተሰጠ ራዕይ ሁለት ገጽታ አለው። በአንድ በኩል "አሮጌው በር" (3:6)፣ "የሸለቆው በር" (3:13) "የጉድፍ መጣያ በር" (3:13)፣ እና "የዘንዶው ን በር" (3: ) አድሶ በቋሚነት ይዘጋል። (3:6፣13፣14)። በሌላ በኩል ደግሞ "የበጉ በር" (3:1, 32)፣ "የአሣ በር" (3:3)፣ "የምንጩ በር" (3:15)፣ "የውሃ በር" (3:26)፣ እና "የፈረስ በር" (3:28) ያድሳል፥ ይከፍታል። (3:1,15,26,26,28)። እንድናስተውለው የሚያስፈልገው ደግሞ "በበጉ በር" ተጀምሮ (3:1)፣ "በበጉ በር" እንዳለቀ ስናይ (3:32) ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት በንስሀና በመመለስ ያደረጉትን ቁርጥ ውሳኔና የገቡትንም ቃል ኪዳን የሚያሳይ ምልክት ነው፡ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር በየዘመናቱ መዝጋትና መክፈት፣ ማሠርና መፍታት፣ መስበርና መፈውስ የሚችል ራዕይ ለሚታዘዙለት መሪዎች ሰጥቶ በእነርሱ በኩል የሚያስደንቅ ሥራውን ሲሠራ ስናየው፣ የራዕዩ ባለቤት እንደሆነ በግልፅ ልናስተውል እንችላለን።

ነህምያ በአመራሩ ዘመን ያጋጠሙትን ተግዳሮቶች በሦስት ዋና ነገሮች ማጠቃለል ይቻላል። እነዚህ ተግዳሮቶችን ስናይ ነህምያ ራዕዩን ከእግዚአብሔር የተቀበለው መሆኑን ብናውቅም፣ እውነተኛ ራዕይ ያለ ተግዳሮት ሊከናወን እንደማይችል የበለጠ ያመለክተናል። አንደኛው ነህምያ ያጋጠመው ተግዳሮት ከውጭ በመጣ ጫና ምክኒያት የሕዝቡ መሰላቸትና መድከም ነው። (ምዕራፍ 4)። በዚህ ጊዜ የወሰደው እርምጃና የሰጠው ምላሽ <u>ፍፁም የሆነ ትሕትና (Humility)</u> ነው። "*አትፍሩአቸው፣ ታላቁንና የተፈራውን ጌታ አስቡ*" (4:14) አላቸው። የራሱን መስዋዕትነት በመግለፅ ራሱን ሊያመጻድቅ አልፈለገም። ከዚህ ይልቅ ዓይኖቻቸውን "*ታላቅና የተፈራውን ጌታ*" እንዲያዩ ሲያበረታታቸው እንመለከታለን።

<u>ሁለተኛው</u> ነህምያ ያጋጠመው ተግዳሮት በይሁዳ ሕዝብ መሀል የፍትህ ጉድለት ጉልቶ መታየትና የአደባባይ ምስጢር መሆኑ ነው። (ምዕራፍ 5) ነህምያ ይህን ግፍ በተመለከተ ጊዜ በምዕራፍ አራት ላይ እንዳየነው ትሕትና ሳይሆን <u>ጽናትና ድፍረት (Courage)</u> በማሳየትና ይህንን የፍትህ ጉድለት በመጋፈጥ ነበር። (5: 6-10)። <u>ራሱንም በምሳሌነት እንዳቀረበላቸው ስናይ የሚናገረውን የሚኖር፣ የሚኖረውን የሚናገር መሪ እንደነበር ልናስተውል እንችላለን።</u> "*አሥራ ሁለት ዓመት ያህል እኔና ወንድሞቼ ለአለቃ የሚገባውን ስንቅ አልበላንም።*" (5:14)፣ "*እኔ ግን እግዚአብ*

*ሔርን ስለ ፈራሁ እንዲህ አላደረግሁም።"* (5:15)፣ "*ከአይሁድና ከሹማምንቱ መቶ አምሳ ሰዎች በገበታዬ ነበሩ።"* (5:17)፣ "*ለአለቃ የሚገባውን ስንቅ አልሻም ነበር።"* (5:18) <u>ሦስተኛው</u> ነህምያ ያጋጠመው ተግዳሮት ከእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል በተነሱት ሳምራውያን በነበሩት የውስጥ ጠላቶች የተነሣው ሲሆን፣ በጣም የተወሳሰበ ና አደገኛ ተግዳሮት እንደነበር መግለጽ አስፈላጊ ነው።

- የሥጋ ግዲያ ሙከራ (Physical Assassination) (6: 1-5)፣
- የስም ማጥፋት ዘመቻ (Character Assassination) (6: 10-14)፣ እና
- የሀሰት ትንቢት በማስተንበይ (False Prophecy) (6: 10-14)

***በነህምያ ላይ የተጋረጡት ተግዳሮቶች ሳይሆን የሚያስደንቀው፣ ነህምያ ለእነዚህ ፈተናዎች የሰጠው ምላሽ ነው፡-***

- የመጀመሪያውን ተግዳሮት የተወጣው <u>ለእግዚአብሔር ሥራ በመጨከንና በመሰ ጠት</u> (<u>Dedication</u>) (6: 2-4)።
- የሁለተኛውን ተግዳሮት የተወጣው <u>የእግዚአብሔርን ፊት በማየትና በመፈለግ</u> (<u>Devotion</u>) (6: 8-9)
- የሦስተኛውን ተግዳሮት የተወጣው <u>መናፍስትን በመለየትና በመመርመር</u> (<u>Discernment</u>) (6: 11-14)!!!
- በቀኑም መጨረሻ ( the bottom line)
  "*ቅጥሩም.... በአምሳ ሁለት ቀን ውስጥ ተጨረሰ!!!"* (6: 15-19)
- ቻርለስ ካውማን እንዲህ ይላል፡- "<u>አብዛኛውን ጊዜ ሕዝቡን ሲመራቸው የነበረ ው መሪ ያለውን ጸጋ አያስተውሉም። ነገር ግን እርሱን ለመምታት በሕይወቱ ዘመን ሲወረውሯቸው የነበሩትን ድንጋዮች ሰብስበው እርሱ ከሄደ በኋላ ለእር ሱ መታሰቢያ ሐውልት ይሠሩለታል</u>።"[42]

[42] Charles Cowman, Oriental Missionary Society, Los Angeles, CA: The OMS, 1928), 258.

## II. አመራር፡- የአዲስ ኪዳን እይታ

### ሀ. የሃይማኖት መሪዎች (ፈሪሳውያን፥ ሰዱቃውያንና፥ ጸሐፍት)፡-

የፈሪሳውያን፣ ሰዱቃውያንና ጸሐፍት አመራር አሉታዊ ተጽዕኖ ያመጣና በታሪክም ጥቁር ነጥብ ጥሎ ያለፈ ስለሆነ በሉቃስ ወንጌል የተገለጸውን በቅርበት ማየታችን ይገባል። ጌታ ኢየሱስ የመረጣቸው አሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት እርሱን በማመንና በመከራውም አብረውት የቆዩ መሆናቸውን እናውቃለን። (ሉቃስ 22፡28-30) ፈሪሳዊያን፣ ሰዱቃዊያንና ጸሐፍት የጌታ ተቃዋሚ ሆነው እንደቆዩና በመጨረሻም ለሞት አሳልፈው በሮማዊያን እጅ እንዲሰጥ ስላደረጉት በኃላፊነት መጠየቅ ያለባቸው መሪዎች ናቸው። እነዚህ መሪዎች በሰባው ዓመት የባቢሎን ምርኮ የተነሡ "መንፈሳዊያን" የነበሩ መሪዎች ናቸው። እየቆዩ ግን አጉል መንፈሳዊነት ውስጥ ከመግባታቸውም በላይ፣ ስለ ራሳቸው ውጫዊ መልክ የሚገዳቸው ስለሆኑ ሕይወትን ከመኖር ይልቅ በተዋናይነት መግለጽ መውደድ ጀመሩ። ይህ ጥልቀት የሌለውና የራሱን መልክ/ ገጽታ ፈላጊ በመሆን ላይ የተመሠረተ አካሄዳቸው፣ በሰዎች ፊትና በራሳቸውም ፊት ተቀባይነት በጥብቅ የሚፈልጉ መሪዎች እንዲሆኑ አስገድዷቸዋል። ሐዋርያው ጳውሎስ "*ራሳቸውን ከራሳቸው ጋር ሲያመዛዝኑ፣ ራሳቸውንም ከራሳቸው ጋር ሲያስተያዩ አያስተውሉም።*" እንዳለው ነው።(2ቆሮ. 10፡12) ከዚህም የተነሣ የእነርሱ ተመልካች/ ታዛቢ ብዙኃኑ ሕዝብ እንዲሆን ስለ ፈቀዱ ብዙ ዓይነት ሀብር ያለው የኑሮ ዘይቤ፥ የተበጣጠሰና ተቃርኖ የሞላበት ሕይወት እንዲኖሩ ተገድደዋል። አንድ ወጥ የሆነ ሕይወትና ኑሮ ያለው ሰው መሆን ያቃታቸው ናቸው።

ይህ ሁኔታቸው እግዚአብሔር ካለው ዓላማ ጋር በቀጥታ የሚጋጭና የሚቃረን ያደርገዋል። እግዚአብሔር በፍጥረት ጊዜ "*ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር።*" (ዘፍ. 126-27) ያለውን ያህል፣ በቤዛነት ጊዜ ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ "*አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኗልና።*" ይላል። (ሮሜ. 8፡29-30፣ ፊል. 3፡21) ስለዚህ ዋና የእግዚአብሔር ዓላማ በፍጥረታችን በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠርነውን ያህል፣ በቤዛነት ያገኘነው ደህንነት ደግሞ የክርስቶስን መልክ እንድንመስል ነው። ስለዚህ የራሳችንን መልክ ልንፈጥር አልተጠራንም። ይህንን እውነት መቀበል ካቃተን ግን እንደ ፈሪሳውያን የራሳችንን

ልክ ለመፍጠር ስንሞክር በራስ መታለል (SELF DECEPTION) ውስጥ እንገባና ራሳችን ተታለን፥ የምንመራውንም ሕዝብ በማታለል እንድንኖር እንገደዳን::

ሰዱቃውያንም እንደ ፈሪሳውያን በምርኮው ዘመን የተነሱና ብዙ ትኩርታቸው የፖለቲካውን የበላይነት መያዝ ስለ ነበር፣ ከሮማውያን ቀጥለው የእስራኤልን ሕዝብ ከባድ ጫና የገዙ ናቸው:: ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ 23፡ 8 ላይ "ሰዱቃውያን ትንሣኤ፥ መላእክትና መንፈስም የለም የሚሉ ናቸው፣ ፈሪሳውያን ግን ሁለቱንም ያምናሉ" ይላቸዋል:: በመንፈሳዊው ዓለም ይህን ያክል ፍላጎት አልነበራቸውም:: የእነርሱ ዋነኛ ጥማት ሥልጣንና ኃይል ላይ ነው:: ጸሐፍት በአንፃሩ "መንፈሳውያን" ከመሆናቸውም ሌላ፣ መጻሕፍትን የመተርጎምና የመተንተን ሰፊና ጥልቅ እውቀት የነበራቸው ናቸው:: (ዮሐ. 5፡ 39)

ፈሪሳውያን፥ ሰዱቃውያንና፥ ጸሐፍት በአንድነት ስናያቸው የሃይማኖት መሪዎች እንደ ነበሩ ብናውቅም፣ የአመራር ባሕርያቸው፣ ስልታቸውና አገላለፃቸው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ካሳየው የአገልጋይነት አመራር ጋር በቀጥታ የሚጋጭና ተቃራኒ የሆነ ነው:: "ጻድቃን" እንደሆኑ በራሳቸው ለሚታመኑና ሌሎቹን ሁሉ በጣም ለሚንቁ.."(ሉቃስ 18:9፣ 10:29፣ 20:20፣ 16:15፣ 18:10-12)፣ ብሎ ሉቃስ ይገልፃቸዋል:: በተጨማሪም ከእግዚአብሔር ይልቅ ገንዘብን በመውደድ የተጠመዱና የተጥመኑት ነበሩ:: (ሉቃስ 11:42፣ 46፣ 20:47) ግብዝነት የሞላባቸውና ወደ ንስሀም ለመምጣት የማይችሉ በራሳቸው ጽድቅ የሚመኩ ናቸው:: (ሉቃስ 12:1-2፣ 11:44፣ 39፣ 16:14-15፣ ወዘተ):: እጅግ ስስታሞችና ሕዝቡን መጠቀሚያ ያደረጉ ጨካኝ መሪዎች ናቸው:: የእግዚአብሔር ጉብኝት የሞላባቸውን የዕዳሎት ዘመናት ያላወቁና ክእጃቸው ያመለጠባቸው ናቸው::(ሉቃስ 19:41-44፣23:34፣20:5፣22:67፣ 11:52፣) እንዲያውም የእግዚአብሔርን ዓላማ ከልባቸው ክፋት የተነሣ በቃልም ሆነ በሥራ ተቃውመውታል:: (16:14-17፣ 4:18፣ 6:20-26፣ 11:43፣ 20:46-47):: በዚህ ሁሉ ክፉ የአመራር ባሕርያቸው ውስጥ ጌታ ኢየሱስ ስለ እነርሱ ሲያነባና ሲፀልይ ስናየው "ስሙም ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል::" የተባለለት እውን ስለሚያደርገው፥ በአመራሩ ሥር ለተቀመጠ ሰው ትልቅ ዕዳሎት ነው!!!

### ለ. የኢየሱስ ክርስቶስ አመራር ሌጋሲ ፡-

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛን ሥጋ ለብሶ በምድር ላይ የተመላለሰባቸው ዓመታት ሰላሣ ሦስት ዓመት ተኩል ቢሆንም፤ በአገልግሎትና በአመራር የምናየው ግን የመጨረሻዎቹ ሦስት ዓመት ተኩል ነው:: የመጀመሪያዎቹ ሰላሣ ዓመታት ያሳ ለፈው ቤተሰቡን በማገልገል ነበር:: (ሉቃስ 2÷ 51-52) ኢየሱስ ሦስት ዓመት ትኩል በማስተማር አገልግሎት የብዙ ሕዝብ ልብ እንደነካ ከአራቱም ወንጌላት ልናይ እን ችላለን:: በቤተ መቅደስ÷ በምኩራብና በሜዳም ያስተምር ነበር::[43] በማስተማር አገ ልግሎቱም በአይሁድ ዘንድ የነበረውን አመራር በላቀና በጠለቀ ደረጃ ሲገልፀው እና ያለን:: ጌታ ኢየሱስ በሕግም ይሁን በነቢያት ዘንድ የተነገርውን ሁሉ ከፍ ባለ ሁኔታ በሕይወት የተረጐመና ያሳየ መሆኑን እንመለከታለን:: ስለዚህም የነበረውን አመራር በብዙ አድናቆትና አክብሮት እንድናይ እንገደዳለን::[44] ጌታ ኢየሱስ የነበረ ውን አገልግሎት ከመግለጻችን በፊት በዚያ ዘመን የነበረውን የጸሐፍት አመራረጥና የነበራቸውም አመራር ዐውድ ማየታችን ይረዳል ብዬ አምናለሁ::

በመጀመሪያ መሪው ወይንም ጸሐፊ የሆነው ሰው አስቀድሞ በእግዚአብሔር ቃል እውቀት የተሞላና የተማረ፤ በአይሁድም ባሕላዊ ታሪክ የተሞላ ሊሆን ይገባዋ ል::[45] ሁለተኛ መሪው ካለው ሰፊ እውቀት የተነሣ ትልቅ ሥልጣን እንዳለው ሰው ይቆጠር ነበር::[46] ሦስተኛ በዚህ መሪ ለመማር የሚፈልግ ማንም ሰው (በተለይም ሕግን ለማጥናት) በመሪው እግር ሥር ተቀምጦ ሊማር ይገባው ነበር::[47] አራተኛ ተማሪዎቹ ከመሪያቸው ጋር የቅርብ ግንኙነት ከማድረጋቸውም ሌላ አብረውት ይጓዙ÷ ይበሉና÷ ወደ ሠርግም አብረው ይሂዱ ነበር::[48] አምስተኛ የመሪው ደቀ

---

[43] Gerald Kittel, ed. *Theological Dictionary of The New Testament,* vol. 2 (Grand Rapids, MI: WM.M. Eerdamns, 1964), s.v. "Didasko," by Rengstorf: 139.
በተጨማሪም:- ማቴ. 4: 23፤ ማር. 6÷ 2፤ ሉቃስ 13÷ 10፤ ማቴ. 26÷ 55፤ ማር. 14÷ 49፤ ሉቃስ 21÷ 37፤ ማቴ. 5÷ 2፤ ማር. 6÷ 34፤ ሉቃስ 5÷ 3 ማንበብ ይቻላል::

[44] Colin Brown, *The New International Dictionary of New Testament Theology*, vol. 3, 115, 766, 767.

[45] Emil Schurer, *A History of The Jewish People in the Age of Jesus Christ, 3* vols. trans. by Sophia Taylor and Peter Christie, (London: T & T Clark, 1885), 320.

[46] Kittel, ed. *TDNT,* VOL. 4, 433.
በተጨማሪም ማቴ. 7÷ 29፤ ማር. 1÷ 22፤ ሉቃስ 4÷ 31-32 ማንበብ ይቻላል::

[47] Ibid., 434. ዮሐንስ 1÷ 37-38.

[48] Cleon Rogers, *"The Great Commission," Bibliotheca Sacra* 130 (July 1973): 264.

መዛሙርት ባሕርያቸው የሚገልጸው ለመሪው የነበራቸው መገዛት ነው::[49] <u>ስድስተኛ</u> የምልጠናው ዘዴ በመሪው እግር ሥር መቀመጥ÷ እርሱን መስማት÷ ጥያቄዎችንም መጠየቅ÷ ምላሹንም በጥንቃቄ መስማትን ያካትታል::[50] <u>ሰባተኛው</u>ና የመጨረሻው ተማሪዎቹ ከመሪያቸው የተማሩትን ትምህርት ለመድገምና ለማስታወስ መቻላቸው ነው::[51]

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለይም በወንጌላት ተገልጸ የምናየው የኢየሱስ አመራር በባሕርይ መቀረፅ÷ በአገልጋይነት÷ እና በሚገለገለው ሕዝብ ላይ÷ ያተኰረ እንደነበር ልንገነዘብ እንችላለን::[52] ጌታ ኢየሱስ የነበረው የከበረ ሕይወትና የአመራር ጥራትና ጥልቀት የደቀ መዛሙርቱን ባሕርይ በመመሥረት÷ በመቅረጽና÷ በማሳደግ ገልጸታል::[53]

ኢየሱስ ከአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርትም በተጨማሪ ሌሎችም ደቀ መዛሙርት ይከተሉት እንደነበረና፣ በኋላም የራሳቸው አገልግሎት እንደ ጀመሩ እናያለን::[54] ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ ያሳለፈው የአሥራ ሁለቱን ሕይወት በመቅረጽ ላይ ነበር:: ኢየሱስ በተደጋጋሚ ጊዜያት "ተከተለኝ" የሚለው ቃል ተጠቅሞ በምናይበት ጊዜ ደቀ መዝሙርነት በባሕርይ ለውጥ የሚገለጽ ተግባር እንጂ፣ እሳቤአዊ የሚያሳይ አልነበረም::[55] ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ የመጀመሪያ ጥሪያቸው ለመስበክ፣ ለማስተማር ወይም ሐዋርያ ለመሆን ሳይሆን፣ <u>ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ ነበር</u>! (ማር. 3፡13-14፣ ሮሜ. 12፡1-2) ጌታ ኢየሱስ ራሱ የትምህርቱ ይዘት እና ትምህርት ቤቱም ነበር:: <u>አገልግሎት የሚጀምረውም ሆነ የሚደመደመው በመሆን እንጂ በማድረግ አይደለም</u>!!! ኢየሱስ በደቀ መዛሙርቱ ፊት በግልም ይሁን በአደባባይ በሕይወቱ ንፅህና፣ "

---

[49] Norman E. Richardson, *The Christ of the Classroom*, (New York: The McMillan Company, 1931), 135; Kittel, ed. *TDNT,* vol. 4, 434-435; Rogers, *"The Great Commission,"* 263.

[50] Kittel, ed. *TDNT*, VOL. 4: 435.

[51] Schurer, *A History of the Jewish People in the Age of Jesus Christ,* vol. 2, 324-325.

[52] በዚህ ሐሳብ ላይ የሚከተለውን ማንበብ ይቻላል:- F. F. Graves, *What Did Jesus Teach?* (New York: The McMillan Company, 1919), 34-35.

[53] A. B. Bruce, *The Training of the Twelve,*(Grand Rapids, MI: Kregel, 1971), 14; ማቴ. 5÷ 17-7÷27፣ 4÷ 23-25፣ 7÷ 28-29.

[54] ...ባዎቹ (ሉቃስ 10÷ 1)፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ የጌታ ወንድም ያዕቆብ (1ቆሮ. 15÷ 7፣ ገላትያ 2÷ 9፣ ዮሐ. 2÷ 12፣ 7÷ 2-10፣ ሉቃስ 6÷ 13-17፣ ማር. 3÷ 13-19፣ ማር. 8÷ 34፣ ሉቃስ 14÷ 27.

[55] See Colin Brown, ed. *The NIDNTT, "Akoloutheo"* by C. Blendinger, 1: 481; Kittel, *"Akoloutheo" in TDNT*, Kittel, 1: 214.

በየዋህነቱና በልቡ ትሕትና" (ማቴ. 11:29)፣ በአመራሩ ጥራትና የአገልጋይነት መን ፈስ (ዮሐ. 13:1-16) ሞዴል በመሆን ራሱን ገልጸላቸዋል:: በተወሰነ መረዳት ብቻ እንዳይረኩና ማደግና መለወጥ እንዳያቆሙ በየጊዜው የላቀውንና የጠለቀውን እንዲ ጠሙ፥ የአመራር አድማሳቸውንም እንዲያሰፉና እንዲያጠልቁ ያደርጋቸው ነበር:: በአንድ በኩል በስኬታማነት እንዳይረኩ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በውድቀታቸውም ተስ ፋ እንዳይቆርጡ አድርጎአቸዋል:: ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የሰጣቸውም ሥልጣን ለእግዚአብሔር ቤት አሠራር ሲባል (FOR THE SAKE OF FUNCTIONALITY) የተሰጣቸው እንጂ፣ የእርከን ሥልጣንና ኃይል ጉዳይ (AN ISSUE OF POWER AND AUTHORITY) እንዳልሆነ በሕይወቱና በአገልግሎቱ በመኖር አሳይቷቸዋ ል:: <u>በእርሱ የተገለጠው ሕይወትና የአመራር ሌጋሲ፣ ልብን የሚያንጠለጥል፥ እስት ንፋስ የሚያቆራርጥ፥ ታይቶ የማይጠገብና ዓይንን ለመክደን የማያስችል ልዩና ክቡር እውነት ነው!!!</u>

የኢየሱስን የአመራር ሌጋሲ ለማየት የምንችለው ለደቀ መዛሙርቱ ስለ ባሕር ይ ለውጥ የሰጠው የጠለቀ ትምህርት (ማቴ. 5-7) በእርጋታና በማስተዋል ስናጠና ው ነው:: እነዚህን ምዕራፎች "የክርስቲያን ባሕርይ" (5:1-12)፣ "የክርስቲያን ተጽዕ ኖ" (5:13-16)፣ "የክርስቲያን ሕይወት እውነታ" (6:1-6፥16-18)፣ "በማስተዋል የሚደረግ የክርስትያን ጸሎት"(6:7-15)፣ እና "የማንኙነት ሥምረት" (7:1-12) በሚ ሉ ዐብይት ሐሳቦች ማካተት ይቻላል:: ለዚህ መጽሐፍ ዓላማ ሲባል ግን "የክርስትያ ን ባሕርይ" (5:1-12) የሚለውን ብቻ እንዳስሳለን::

ብዙ ከመሄዳችን በፊት ልናነሣቸው የሚገቡን ሦስት ጉዳዮች አሉ :- የተነገራቸ ው ሰዎች፣ በውስጣቸው የታየው መልካም ነገሮች፣ እና የተሰጣቸው የበረከት ቃል ኪዳን:: <u>አንደኛ</u> የተነገረላቸው ሰዎች ስምንት የተለየዩ ዓይነት ሰዎች ሳይሆኑ፣ ስምን ት ዓይነት መልካም ባሕርያት ያላቸው አንድ የደቀ መዛሙርት ቡድን ነው:: <u>ሁለተኛ</u> በውስጣቸው የታየው መልካም ነገር በተመለከተ ጌታ ኢየሱስ ሁለት ዋና ነገሮችን ጠቅሷል:-

- *"በመንፈስ ድሆች የሆኑ"* (5:3)
- *"ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ"* (5:6)

እዚህ ላይ የገለፃቸው "ድህነትና ረሃብ" ግን ሥጋዊ ሳይሆኑ፣ መንፈሳዊ ድህነትና ረሃብን ለማሳየት ብሎ ነው:: <u>ሦስተኛ</u> የተሰጣቸው የበረከት ቃል ኪዳን "ብፁዓን ናቸ ው" በሚል ገልጾታል:: ምንም እንኳን "ብፁዓን ናቸው" (በግሪክ "MAKARIOS")"

ደስተኛ" ወይም "ደስታ" ማለት ሊሆን ቢችልም፤ በዚህ ክፍል ለተገለጸው ሐሳብ እውነት የራቀ ትርጉም (SUBJECTIVE) ያደርገዋል። ጌታ ኢየሱስ የሰጠው የበረ ከት ቃል ኪዳን በእነርሱ ስሜት የሚለካና የሚመጠን "ደስታ" ሳይሆን፤ እግዚአብ ሔር ስለ እነርሱ በሚያስበው ሐሳብ ላይ የተመሠረተ "በረከት" ነው። ይህን መግቢያ ሐሳብ ለማጠቃለል ጌታ ኢየሱስ በማርቆስ 12:29-31 አሥሩን ትዕዛዛት/ ሕጎች ሁለት እንዳጠቃለላቸው፤ እነዚህንም ስምንቱ ባሕርያት የመጀመሪያ አራቱ ከእግ ዚአብሔር ጋር፤ ሁለተኛዎቹ አራት ደግሞ ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለንን ግንኙነት ያመለክታሉ።

## <u>የክርስቲያን አገልጋይ ባሕርያት (ማቴዎስ 5: 3-12)</u>:-

1. "*በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው።* (ቁ. 3)

እግዚአብሔርን ስለ ምንም ነገር ማስገደድ፥ ማለትም ራሳችንን ማ ፅን፥ መርዳት፥ ወይም መምራት ስለማንችል፤ በእርሱ ላይ ያለን ትሑት መደገፍ እንገልጽለታለን። ስለ ትልልቅ ነገሮች ብቻ ሳይሆን ትንንሽ ስለሚ መስሉም ጉዳዮች "በመንፈስ ድሀ" ሆነን እንገልጽለታለን። (ኢሳ 41: 17-18) በሌላ መልኩ በኢሳይያስ 57:15 ላይ "የተቀጠቀጠና የተዋረደ መንፈስ ካለው ጋር በከፍታና በተቀደሰ ስፍራ እቀመጣለሁ" እንዳለው ዓይነት ነው። (ኢሳ 66: 1 -2) በቀድሞ ዘመን በኮሌጅ በነበርኩበት ጊዜ HERMENEUTICS አስተምሮኝ የነበረው <u>ዶ/ር ጎርደን ፊ</u> በአንድ ጽሁፉ ላይ፦ "<u>እግዚአብሔር አምላክ ስለሆነ ምንም ነገር ማድረግ አይኖርበትም፤ ነገር ግን ደግሞ ያደርገዋል፤ ምክኒያቱም የጸጋ ሁሉ አምላክ ስለሆነ</u>።"("GOD DOES NOT HAVE TO DO ANYTHING, BECAUSE HE IS GOD; BUT HE DOES IT ANYWAY, BECAUSE HE IS GRACIOUS.")

የእግዚአብሔር መንግሥት የተሰጠው ለድሆች እንጂ፤ ለሀብታሞች አይደለም፤ ለትንንሽ ሕፃናት እንጂ፤ (ማቴ. 11:25፤ ሉቃስ 10:21) በራሳቸው ኃይል ድልን ለመቀዳጀት ለሚዘጋጁ ወታደሮች አይደለም፤ ለደካሞችና ሸክማቸው ለከበደባቸው እንጂ፤(ማቴ.11:28) በኃይላቸው፥ በሥልጣናቸውና በእውቀታቸው ለሚመኩት አይደለ ም።

- ፊሪሳውያን፥ ሰዱቃውያንና ጸሐፍት በራሳቸው ጽድቅ የሚመኩና የጨበጡ ት የሚመስላቸው::
- ቀናተኞች በራሳቸው ኃይልና ጉልበት የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚያ መጡ የመሰላቸው::

- "ቀራጮችና ኃጢአተኞች" (ሉቃስ 15:1-2) ሰው በስያሜ የለደፈባቸው፤ ሐዋር ያው ጳውሎስም "ደካሞች፤ ያልከበሩ፤ የምናፍርባቸው" የሚላቸው(1ቆሮ. 12:2 2-25) በእግዚአብሔር ጸጋና ምሕረት ከመደገፍ በስተቀር ሌላ መታመኛ የሌላ ቸው ናቸ ው:: በእግዚአብሔር ፊት በፍፁም በታመንና መደግፍ ትሑት በሆነ መንፈስ ለሚገልጹት ጌታ የሰጣቸው የበረከት ቃል ኪዳን "መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና::" የሚል ነው:: ጌታ ኢየሱስ በሌላም ሥፍራ "አባቴ እንደ ሾመ ኝ እኔ ደግሞ በመንግሥቴ ...ለመንግሥት እሾማችኋለሁ::" ይላል:: (ማቴ 22:2 8-30)

## 2. "*የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው*" (ቁ. 4)

እነዚህ የነበራቸውን ቅንነት ሲገፋና መጠቀሚያ ወይም የሥልጣን እርከን መወ ጣጫ ሲሆን፤ የሕይወታቸው ጽድቅና የኑሮአቸውም ቅድስና ሲረገጥ፤ የነበራቸው ሰብዓዊ መብትና ክብርም በክርስትናቸው ምክኒያት ሲረገጥና ሲጠቃ አይተው "የሚ ያዝኑ ብፁዓን ናቸው::" <u>ለክርስቲያን፤ በተለይም ለመሪዎችና ለአገልጋዮች እንባ ማፍሰስ/ ማልቀስ የድካም ምልክት ሳይሆን፤ የብርታት ምልክት ነው</u>! ኢየሱስ ራሱ በተደጋጋሚ ጊዜያት እንባውን ሲያፈስ እንመለከታለን:- የማርያምን እንባ አይቶ አልቅሷል (ዮሐ. 11:32-35)፤ ስለ ኢየሩሳሌም ከተማና ስለ መሪዎቿም አልቅሷል (ሉቃስ 19:41-44፤ 13: 34-35):: ለእንዲህ ዓይነት ሰዎች የሰጣቸው የበረከት ቃል ኪዳን "*መጽናናትን ያገኛሉና::*" የሚለው ቃል ነው::

## 3. "*የዋሆች ብፁዓን ናቸው*" (ቁ. 5)

"የዋህ" የሚለው ሐሳብ በግሪክ ተውሳከ ግሥ "ፕራኦስ" የሚል ሐሳብ ሲሆን፤ ትርጓሜውም:- "የሰከነ"፤ "ትሁት"፤ "ሌላውን ሰው የሚያስብ"፤ "መልካም ጠባይ ያለው፤"ሌላውን ሰው የሚያስቀድም" ማለት ነው:: እንዲህ ዓይነቱ ሰው የራሱን መንፈስ መግዛትና መቆጣጠር የሚችል ስለሆነ ነው እላይ የተጠቀሱት ነገሮች ማድ ረግ ይችላል:: ከዚህም በላይ "የዋህነት" የሚለው ቃል የጠለቀ ትርጉመ ወሰን ያለው

ጉዳይ ስለሆነ በግሪክ ቋንቋ የተነገረውን ፅንሰ ሐሳብ ማየት በጣም አስፈላጊ ነው።
ጌታ ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል 11፡ 29 ላይ "*ከእኔ ተማሩ፤ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፤*" ብሎ ከተናገረው ሐሳብ በመነሣት፥ "የዋህነት ወይም ትሕትና" በግሪክ ቃሉ ትርጉሙ ወሰኖች እንዳሉት እንመለከታለን፦

- "የራስን አስፈላጊነት ለአንድ አፍታ እንኳን ለማሰብ አለመፈለግና ስለ ራስ ማንነት ለማሰብ አለመፈለግ"
- "የራስን መብት ለሌላው ሰው ጥቅም ሲባል ለመሰዋት ፈቃደኛ መሆንና ማድረግ"

ልብ እንድንል የሚያስፈልገው "የዋሆች ብፁዓን ናቸው" የሚለው ሐሳብ "የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው" (ቁ. 4) በሚለውና "ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው" (ቁ. 6) በሚሉት ሐሳቦች መካከል መገለፁ ነው። በእግዚአብሔር ፊት ጉስቁልናችንን ለመናገርና እኛም በፊቱ ኀስቋሎች መሆናችንን ለመቀበል በጣም ቀላል ነው። ነገር ግን ሌሎች ሰዎች ያንኑ በጌታ ፊት የገለጽነውን ጉስቁልና እንዲናገሩን መፍቀድ፤ ከሌሎችም አፍ መስማት በጣም ከባድ ነው። ያመናል! "የዋህነት" ሲኖረን ብቻ ነው ስለ ራሳችን ያለን መረዳት በእውነት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን የሚያደርገው።" "የዋህ" የሆነ ሰው እግዚአብሔርም ሆነ፥ ሌላ ሰው ስለ እርሱ አንድ ዓይነት አስተያየት ያላቸው መሆኑን አይቶ የሚደነቅ ነው!!!

ጌታ ኢየሱስ የሰጣቸው የበረከት ቃል ኪዳን "*ምድርን ይወርሳሉና*" የሚል ቃል ነው። እንደ ሰው አስተሳሰብ ቢሆን የተቃራኒው ሊሆንባቸው ይገባ ነበር፤ ምክኒያቱም በሰው የተረገጡ ይመስላሉ፤ ናቸውም። በእግዚአብሔር ፊት ግን ትልቅ ዋጋ ያላቸው ናቸው!!! (1ቆሮ. 3፡18-23፤ መዝ. 37፡1፣11፣ 22፣ 34)

- ***ይህንን ሐሳብ ለማጠቃለል "የዋህነት" ወይም "ትሕትና" በውጭ የሚገለፅ ብቻ ሳይሆን የውስጥ ውበት ነው!!!***

4. "***ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው።***" (ቁ. 6)

የጌታችን እናት የሆነችው ማርያም በሉቃስ 1፡53 ላይ "*እግዚአብሔር የተራቡትን በበጎ ነገር አጥግቧልና*" ትላለች። "ጽድቅ" በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ቢያንስ ሦስት ገጽታዎች አሉት።

❖ "ሕጋዊ ጽድቅ" በእግዚአብሔር ጸጋና ምሕረት ምክኒያት በፊቱ ትክክለኛ የግንኙነት ሥምረት እንዲኖረን ያደረገው ትልቅና ክቡር ሥራ ያመለክታል። (ሮሜ. 3፡21)

❖ "ሞራላዊ ጽድቅ" እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና የሚያስከብር ባሕርይና ጠባይ መያዝን ያመለክታል።

❖ "ሕብረተ-ሰብአዊ ጽድቅ" በአመፅና በግፍ የተረገጡትንና የተጠቁትን ሰብዓዊ መብታቸው እንዲጠብቅና ክብራቸውም እንዲመለስ በሕጋዊ ፍርድ ቤቶች፤ አመራርና አስተዳደር ጋር በመነጋገር፤ ፍትሐዊ በሆነ የንግድ ልውውጥና በጋብቻና በቤተሰብ ውስጥ ፍትሐዊ አመራር እንዲኖር አዎንታዊ ጫና በመፍጠር ከቅን ልብ የወጣና ከበጎ ሕሊና የመነጨ እውነተኛ ለሆነ ነገር መቆምን ያመለክታል። እንዲህ ዓይነቱ አሠራር ትክክለኛ ገጽታው የሚገለፀው "ጽድቅን ስንራብና ስንጠማ" ብቻ ነው!!!

5. "*የሚምሩ ብፁዓን ናቸው*" (ቁ. 7)

"ምሕረት" የጠለቀ ፍላጎት ላላቸው ሰዎች የተለየ ርኅራኄ ማሳየትን ሲያመለክት፤ የግሪኩ ቃል "ኤሊዕስ" በኃጢአት ምክኒያት የመጡትን ስቃይ፥ ጉስቁልናና፥ ውድቀትን አይቶ መራራትን ያሳያል። በአንፃሩ "ጸጋ" ደግሞ በግሪክ "ካሪስ" የሚል ሆኖ፥ ዋናው ሥር በሆነው በኃጢአትና በሕሊና ወቀሳ ላይ ትልቅ ሚና የሚጫወት ነው። በጣም የሚያስደንቀው የዋሆች ናቸው ራሳቸው ምሕረት የተቀበሉትን ያህል ለሌሎች ምሕረት ሊያሳዩ የሚችሉት።

6. "*ልበ ንፁሆች ብፁዓን ናቸው*" (ቁ. 8)

የልብ ንጽሕና መተርጎም ያለበት ከምንም ዓይነት ብክለት (DEFILEMENT) የተጠበቀና የውስጥ ልባዊ ቅንነትን ከመሆኑ እንጻር ሊሆን ይገባል።

❖ ዳዊት፡- (መዝሙር 24፡3-4፤ 51፡6፡ 10፡ 27፡8፤ 19፡14)

❖ ፈሪሳዊያን፡- (ሉቃስ 11፡39፤ ማቴ. 23፡25-28)

"*ልበ ንጹሖች*" ፡-

❖ በጠቅላላ የግልም ሆነ የአደባባይ ሕይወታቸው በእግዚአብሔር ፊትና በሰው የተደበቀ የሌላቸው (TRANSPARENT) ሰዎች ናቸው። ልበ ንፁሆች እንደ ተከፈተ መጽሐፍ የሚነበቡና ልብን የሚያሳርፉ ናቸው።

- ልባቸውም፥ ማለትም ሐሳባቸውና ውስጣዊ መንስኤ (MOTIVE) ንጽሕና እድፋም ከሆነ ስውር ግላዊ ፍላጎት እጅግ የራቁ ናቸው::
- በፊታቸውም ግብዝነት፥ ፈሪሳዊነትና፥ ማታለል እጅግ የተጠሉና የተናቁ ናቸው:: እንዲህ ዓይነት ሰዎች "*እግዚአብሔርን ያዩታል::*"

7. "***የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው***" (ቁ. 9)

ከልብ ንጽሕና ወደ "የሚያስተራርቁ" የሚለው ሐሳብ መሸጋገሩ የሐሳብ ፍሰት እንዳለ ያመለክታል:: ምክኒያቱም የልብ ንጽሕና ያላቸው ሰዎች ብቻ ናቸው በሰዎች መካከል የእርቅን መንፈስ ሊያመጡ የሚችሉና የሰላም መልዕክተኛ መሆን የሚችሉ:: ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው "*ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ::*" (ሮሜ. 12፡18) አንዳንዴ የማይቻልበት ጊዜ እንዳለ ብናውቅም፤ "*በእኛ በኩል*" ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ልንሆን ተጠርተናል:: ሌላውን ሰው (የበደለንን) ለመቆጣጠርና ለመለወጥ ባንችልም፤ በእኛ በኩል ግን ራሳችንን ለመቆጣጠርም ሆነ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለመለወጥ እንችላለን:: *ሆኖም ግን "በሰላም መኖር" ምንም ዓይነት ዋጋ ተከፍሎና እውነት ተለባብሶ መኖር (APPEASEMENT) አይደለም:: አለበለዚያማ የእግዚአብሔርን ጸጋ ርካሽ እናደርገዋለን::*

- ሰላምን መፍጠር በስቃይ ውስጥ፡-
- የጐዳነውና የበደልነውን ሰው ይቅርታ ስንጠይቅ፤
- የጐዳንን እና የበደለንን ሰው ስንገስፅም፤
- የበደለን ሰው ይቅርታ እስከሚጠይቅ ድረስና ንስሀ እስኪገባ ድረስ የልብ ስቃይ፤ የመስማት ስቃይ፤
- ተቃራኒ ሐሳብ ካላቸው ሰዎች ጋር ስንጋፈጥም፤
- በቅንነት ያደርግነው በሌላ ሲተረጎም፤ ያደረግነው መልካም ነገር እጃችንን የሚያስነክስ ሲሆንና፤ ሰዎች ሊረዱን ሲያቅታቸው:: በእነዚህ ሁሉ በሰላም ለመኖር ስንል የሚያጋጥመን ስቃይና የምንከፍላቸው ዋጋዎች ናቸው::
- አጥብቀን ልናስተውለው የሚገባን ግን ንጽሕና ከሌለው ዶክትሪንና ንጽሕና ከሌለው አንድነት ልንጠበቅ እንደሚያስፈልግ ነው:: ከዚህም በላይ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታርቅ ስንል የሕይወት መሰጠት ከሌለውና ደቀመዝሙርነት

ን አጥብቆ ከማይወስድ የወንጌል ሥርጭትም ልንጠበቅ ይገባል:: የእግዚአብሔር ልጅነታችን የሚታወቀውም በዚህ ነው::

8. "*ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው*" (ቁ. 10)

ሰላምን ከመፍጠር ወደ "መሰደድ"፣ ከማስታርቅ ወደ መገፋት፣ የሚገርም ሽግግር ነው:: "ስለ ጽድቅ" (ቁ. 10) እና "በእኔም ምክኒያት" (ቁ. 11) የሚሉት ሐሳቦች የበለጠ ነገሩን የጠራና ምክኒያት እንዳለው ያደርገዋል:: "መሰደድ" ምንም ጊዜም ሊታረቁ የማይችሉ ሁለት ተቃራኒ የሆኑ የኑሮ ዘይቤዎች የግጭት ውጤት ነው:: ጌታ ኢየሱስ እንዳለው:- "*ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ:: ሐሴትም አድርጉ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያት እንዲሁ አሳድደዋቸዋልና*" (ቁ. 12) ስደት፥ መከራና ስቃይ "*ስለ ጽድቅ*" እና "*በእርሱም ምክኒያት*" በክርስቲያን፣ ይልቁንም በመሪዎች ላይ ሲደርስ የደቀ-መዝሙርነት ምልክታቸው፣ መብታቸውና ግዴታቸው ነው!

## ሐ. የሐዋርያው ጳውሎስ አመራር:-

አዲስ ኪዳን የሐዋርያው ጳውሎስ መለውጥ ስድስት የተጨመቁ ታሪኮችን ያካትታል:- ሦስቱ በሐዋርያት ሥራ (9:20-22፣28-29፣1-30፣ 22:1-21፣ 26:1-23)፣ ሦስቱ ደግሞ በሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክቶች (ገላትያ 1:3-17፣ 1ቆሮ. 158-10፣ ፊል. 3:4-11፣ ሮሜ 10:2-4፣ ኤፌ. 3:1-13፣ ቆላ 1:23-29):: የመጀመሪያዎቹ ጥቅሶች የሚያመለክቱት የጳውሎስ መለወጥ እውነተኛ ታሪክነቱ ሲተርኩ፣ ሁለተኛዎቹ ደግሞ ጳውሎስ በተቃዋሚዎቹ ፊት የነበረውን ክርክር ፀጥ ለማሰኘት ያቀረበው የሚሞግት አቀራረብ (APOLOGETIC) ነው::

ሐዋርያው ጳውሎስ ለአሕዛብ የተጠራ ሐዋርያ የነበረ ለመሆኑ በመጀመሪያ ለሐናንያ በተነገረው የጌታ መልዕክት (የሐዋ. ሥራ 9:15)፣ ከዚያም "*በሰው ሁሉ ፊት*" (የሐዋ. ሥራ 22:15)፣ ቀጥሎም "*...ሂድ፥ እኔ ወደ አሕዛብ ከዚህ ወደ ሩቅ እልክሃለሁና አለኝ::*" (የሐዋ. ሥራ 22!7-21) በሚሉ ሐሳቦች ተገልፆ እናየዋለን:: ሐዋርያው ጳውሎስ ራሱም "እንግዲህ ይህ የእግዚአብሔር ደህንነት ለአህዛብ እንደ ተላከ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን፣ እነርሱ ደግሞ ይሰሙታል::" (የሐዋ. ሥራ 28:28) "*ስለዚህ ከሰማይ የታየኝን ራዕይ እንቢ አላልኩም::*" (የሐዋ ሥራ 26:19-

20) የሐዋርያው ጳውሎስ ሐዋርያነት በተመለከተ ብዙ መጻሕፍቶች እና መጣጥፎች እንደተፃፉ አውቃለሁ:: በእርግጥ ጳውሎስ ራሱ የሐዋርያነት ሥልጣኑን ማስረገጡ ብቻ ሳይሆን፣ በአገልግሎቱ ዘመናትም ሲገልፀው እናያለን:: ልናነሳቸው የሚገቡን ጥያቄዎች እንዳሉና ልንመልሳቸውም እንደሚገባ ማወቁ አስፈላጊ ነው ብዬ አምናለሁ:: ሐዋርያ ማለት ምን ማለት ነው? ጳውሎስ ሐዋርያነቱን ለማስረገጥ ምን አስገደደው? በምን ዓይነት ውስጥ በነበረበት ጊዜ ነው ሐዋርያ እንደሆነ ለማስረዳት የፈለገው? የሐዋርያነት ሥልጣኑን የተለማመደው ስለ ራሱ ከነበረው መረዳት ጋር እንዴት አስታረቀው?

"ሐዋርያ" ("APOSTLE"):- በግሪክ "አፖስቶሎስ") የሚለው ስያሜ በአዲስ ኪዳን በተለያዩ ገጽታዎች ተገልፆ እናገኘዋለን:: ሔርማን ክረመር "ሐዋርያ" ስለሚለው ቃል ሲፅፍ:- "አብዛኛውን ጊዜ በተለየ ትኩረት የተጠቀሰው በቅፅል (ADJECTIVE) መልክ 'የተላከ'፣ ከዚህ ሌላ በመጠነ-ሰፊነቱ (SUBSTANTIVE) "የተላከ'፣ 'ሐዋርያ'፣ 'አምባሳደር' ማለት ሊሆን ይችላል" ይላል::[56] በመጀመሪያ ደረጃ ጌታ ኢየሱስ የደነገገውን ቢሮ ሲያመለክት (ሉቃስ 6÷ 12-13)፣ በሁለተኛ ደረጃ ለዚህ የተጠሩ ሰዎችያላቸውን የሐዋርያነትን ሥልጣን ያመለክታል:: (ማር. 3÷ 13 -19፣ ዮሐ. 17:18፣ ሮሜ 10: 15)

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን በምናጠናበት ጊዜ በአንድ በኩል የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን መወለዷና ዕድገቷን ስንመለከት፣ በሌላ በኩል ደግሞ የክርስቶስ ጠላት የሆነው ሰይጣን ገና ከጅምሩ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ሲጥር የምናይበት ትዕይንት ነው:: የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ አንድና ሁለት የመንፈስ ቅዱስን ታላቅ ሥራ ስናይ፣ በምዕራፍ ሦስት እስከ ስድስት ደግሞ የሰይጣን መንፈስ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመቋቋም ሲሞክር እንመለከታለን:: "በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ" (4:8) የሚለውና ሐናኒያ "በሰይጣን መንፈስ ተሞልቶ" (5:3) የሚለው ሐሳብ እላይ ያልነውን ሐሳብ ይገልፃል:: ሰይጣን ገና እያደገች ያለችውን የመጀመሪያይቱን ቤተ ክርስቲያን (አዲሱን ሕብረተ ሰብ) ለመገዳደር የሞከረው ሦስት ዓይነት ገጽታ ያላቸው ፈተናዎችን በማምጣት ነው::

ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት <u>የመጀመሪያው ፈተና ስደትና መከራ በማምጣት፣ ከዚያም በውጭ ጫና በማምጣት፣ በኋላም ያልተሳካለት መሆኑን ሲያይ የአንዳንዶቹ</u>

[56] Hermann Cremer, *Biblioco-Theological Lexicon of New Testament Greek*, (Edinburgh: T & T Clark, 1895) 530.

ን ሞራል ከውስጥ እንዲላሽቅ በማድረግ፣ በመጨረሻም ሐዋርያት የነበራቸውን የሐዋርያነት ጥሪ በማዛባት "ለቃሉና ለጸሎት" ከመስጠት ይልቅ፣ በሌላ ጉዳይ ማለትም ምግብ በማደል ሥራ ውስጥ እንዲሠማሩ ፈተናን በማምጣት ነበር። ሐዋርያት የነበራቸውን ቅደም ተከተል ቢያዛንፉ ኖሮ፣ የመጀመሪያይቱ ቤተ-ክርስቲያን ለብዙ የሐሰት ትምህርቶች የተጋለጠች ትሆን ነበር። እዚህ ላይ በአጽንዖት መጠቀስ ያለበት ጉዳይ ምንም እንኳን ሐዋርያትና ፓስተሮች በመጋቢነት/ እረኝነት አገልግሎታቸው የሚመሳሰሉ ቢመስሉምና ቢሆኑም፣ ፓስተሮች ግን ሐዋርያት አይደሉም። ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን የምትቆምበትን መሠረት የሚጥሉ፣ የእግዚአብሔርን ቃል መለኪያም የሚያቆሙ ሲሆኑ፣ ፓስተሮች ደግሞ በሐዋርያት የተሰጠውን ትምህርት የክርስቶስን አካል ለማነፅና ለማሳደግ በስብከትና በማስተማር አገልግሎታቸው የሚገልጹና የሚያስተላልፉ ናቸው።

ሐዋርያው ጳውሎስ በጣም የሚያስደንቀው የሐዋርያነት ሥልጣኑንም ሆነ ልምምዱን የገለጸበት ዐውድ በቅንነትና በፍፁም ትሕትና በተሞላበት መንፈስ ነው። በ2ቆሮንቶስ ምዕራፍ 10÷1 ላይ፦ "*እኔም ራሴ ጳውሎስ በእናንተ ዘንድ ፊት ለፊት ሳለሁ ትሁት የሆንሁ ከእናንተ ግን ብርቅ የምደፍራችሁ በክርስቶስ የዋህነትና ገርነት እመክራችኋለሁ።*" ይላል። ቀጥሎም "*ጌታ እናንተን ለማነፅ እንጂ እናንተን ለማፍረስ ያይደለ በሰጠው በሥልጣናችን ከፊት ይልቅ ብመካ እንኳ አላፍርም።*" ይላል።(2ቆሮ. 10÷8) ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ራሱ ያለው መረዳት የጠለቀ መሆኑን ከገለጻቸው ሐሳቦች ማስተዋል ይቻላል።

- "*<u>ከኃጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ።</u>*" (1ጢሞ. 1÷15)
- "*ይህ ጸጋ <u>ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ ለማንስ ለእኔ ተሰጠ</u>።*" (ኤፌ. 3÷9)
- "*ከሁሉ በኋላ እንደጭንጋፍ ለምሆን ለእኔ ደግሞ ታየኝ። <u>እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝና</u>።*" (1ቆሮ. 15÷8)

ሐዋርያው ጳውሎስ የሐዋርያነት ሥልጣኑን በሚለማመድበት ጊዜ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ከሰጠው የማጠቃለያ ሐሳብ (የሐዋ. ሥራ 20÷1-38) የአገልግሎቱን ገፅታ የሚያሳዩ ሦስት ዋና ነገሮችን ማየት እንችላለን። <u>በመጀመሪያ</u> ሐዋርያው ጳውሎስ ይሰጠው የነበረው ትምህርት የነጠረና ሙላት ያለው ነበር። (የሐዋ. ሥራ 20÷20-25) <u>ሁለተኛ</u> ጳውሎስ ሁሉንም ሰው ለመድረስ በብዙ ትጋት ደክሟል። (የሐዋ. ሥራ 20÷20-21) "በእስያም የኖሩት ሁሉ አይሁድም፣ የግሪክ ሰዎችም የጌታን ቃል እስኪሰሙ ድረስ ሁለት ዓመት ያህል እንዲህ ሆነ።" (19÷10)

ሦስተኛ ጳውሎስ የተጠቀመው ዘዴ ደግሞ:- "*...በትህትና ሁሉና በእንባ... ለጌታ እየተገዛሁ...በጉባኤም በየቤታችሁም አወራሁላችሁና አስተማርኋችሁ...*" ይላል:: (20÷19-21)

ጳውሎስ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች በገላትያ መልዕክትና በሁለተኛ ቆሮንቶስ የሐዋርያነቱን ጉዳይ አስረግጦ ሲናገር እናየዋለን:: እንዲህ ለመናገር ያነሣሣው ነገር ምንድነው? ብለን መጠየቅ ይኖርብናል:: እንዲህ እንዲናገር መነሻ የሆነው አንዳንዶች ሐዋርያ አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ከሆነም ከሁሉም ያነሰና የጐደለ አድርገው ይናገሩ ስለነበረ ነው:: ጳውሎስ ለዚህ ምላሽ ሲሰጥ በሐዋርያነት ጥሪው ከጴጥሮስ ጋር እኩል እንደሆነ፣ የሚለያዩበት ነገር ጴጥሮስ ለአይሁድ እንደተጠራና ጳውሎስ ደግሞ ለአህዛብ የመጠራቱ ጉዳይ እንደ ነበር ገልጿል:: (1ቆሮ. 9÷1፣ 15÷8-11፣ 2ቆሮ. 12÷12፣ 11÷5) ከአንድ ሐዋርያ የሚጠበቀውም ምልክቶች፣ ተአምራትና ፈውሶች እንዳከናወነም በግልፅ አስቀምጦታል:: (የሐዋ. ሥራ 16÷16-24፣ 19÷11-20፣ 2ቆሮ. 12÷12)

እነዚህን ሐሳቦች ማየታችን ጳውሎስ በሐዋርያነቱ የሚመካ እንደ ሆነ ለማሳየት ሳይሆን እንዲያውም የሐዋርያነት ጸጋው በብዙ ትህትና እንደያዘው ለመግለፅ ነው:: ጳውሎስ ሐዋርያነቱ የእርከን መወጣጫ፣ የሥልጣንና የኃይል መመኪያ አላደረገውም፣ በሚያገለግለውም የእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ሊሰለጥን ራሱን አልፈቀደም:: (2ቆሮ. 1÷24) የሐዋርያነት ጸጋውም ለሕዝቡ ሲባል እንደተሰጠውም ያውቃል:: (ቆላ. 1÷25) ክርስቶስና መስቀል ካልሆነ በስተቀር ሌላ ትምክህት እንደሌለውና (1ቆሮ. 2÷2)፣ ቢመካም ከድካሙ በቀር ለሌላ እንደማይመካ ይናገራል:: (2ቆሮ. 11÷30-31፣ 12÷1-10) <u>በሌላ በኩል ደግሞ የጳውሎስ ሐዋርያነት በእግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ በሰው ፈቃድ አልመጣም::</u> (የሐዋ. ሥራ 13÷1-3፣22÷21፣ 16÷6-10፣ 18÷9-10፣ 19÷21፣ 23÷11፣ 27÷23-25፣ 9÷15-16፣ ወዘተ.) በተጨማሪም ሐዋርያነቱ በእግዚአብሔር ኃልና ክብር የተሸበበ ነበር:: (1ቆሮ. 2÷4-5) ከዚህም ሌላ በሐዋርያነቱ ምክኒያት በብዙ መስዋዕትነት መከራና ሥቃይን የተቀበለ ነበር:: (2ቆሮ. 11÷22-29) በዚህ ሁሉ ተቃውሞ፣ መከራና ስደት መሀል ግን "*ማንም ሳይከለክለው የእግዚአብሔርን መንግሥት እየሰበከ ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ ገልጦ ያስተምር ነበር::*" (የሐዋ. ሥራ 28÷31)

**መ. የመጀመሪያይቱ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን:-**

በአዲስ ኪዳን ላይስንመለከት ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን የምትቆምበት መሠረ ት ለመጣልና ለመመሥረት ከነበራቸው ሥልጣን ሌላ፣ ስለ "ሥልጣን" ጉዳይ የተለየ ትኩረት ሲሰጠው አናይም። የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪዎቻቸውን እንዲያከብሩና እንዲገዙ ቢያዝም (ዕብ. 13÷17፤ ፊል. 2÷20-21፤ 25-30)፣ ትኩረቱ ግን በነበራቸ ው ሥልጣን ሳይሆን፣ ሕዝቡን በመመገብና በመንከባከብ ስለሚደክሙ ነው። ከዚህ የተነሣ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንም ይሁን፣ በዓለም አቀፏ ቤተ ክርስቲያን (በጊዜው የነበረው ዓለም) ምንም ዓይነት የቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር መዋቅር እንደነበረ በግልፅ የምናየው ነገር የለም። ስለዚህም በአዲስ ኪዳን የሥልጣን፥ የኃይልና የአስተ ዳደር መዋቅር ዋና የትኩረት አቅጣጫ አልነበረም!!!

በመጀመሪያይቱ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አራት ዓይነት ሽግግሮችና ለውጠ ች እንደነበሩ መጥቀሱ የሚገባ ይመስለኛል። አንደኛው የጂኦግራፍ ለውጥ (GEOGRAPHICAL CHANGE) ነው። ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ላይ እንደገለፀው የመጀመሪያቱ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን የተጀመረችው በኢየሩሳሌም ሲሆን፣ የደ መደመችው ግን በሮም ነው። (የሐዋ. ሥራ 1:8፤28:28-31) ሁለተኛው የብሔር ለውጥ/ሽግግር (ETHNIC CHANGE) ነው። የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ስትጀምር በአይሁድ ሕዝብ ይሁን እንጂ፣ በኋላ ግን አሕዛብን ሁሉ የምታካትት ቤተ ክርስቲያ ን ሆናለች። (የሐዋ. ሥራ 8:10፤15)። ሦስተኛው ደግሞ ሰዎች ወደ ኢየሱስ ክርስቶ ስ እምነት በሚመጡበት ጊዜ የአመለካከት ለውጥ (CULTIC CHANGE) ስለ ነበር፣ አሕዛብ ወደ ጌታ ሲመጡ በመገርዝ በአይሁድ ልማድ ሳይሆን በእምነትና በንስሀ እንደሆነ ሐዋርያት በምዕራፍ 15 ላይ ውሳኔአቸውን በግልፅ አስቀምጠዋል። (የሐዋ. ሥራ 15:1-35) አራተኛው የአምልኮ ቦታ ለውጥ (TEMPLE = SYNAGOGUE = ANYWHERE) ስለ ነበረ፣ የአምልኮ ሥፍራ ከቤተ መቅደስ ወጥቶ ወደ ምኩራብ፣ ከዚያም በየትም ቦታ መደረግ እንደ ተጀመረ እናያለን።

እላይ የጠቀስኳቸው አስፈላጊ ጉዳዮች ወደ ስዕሉ ማምጣታችን የመጀመሪይቱ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ምን ያህል ፈጣን በሆነ ሽግግር እንደነበረችና፣ በዚያ መጠንም "የሥልጣንና የኀይል ጥያቄ" ጥያቄዋ እንዳልነበረ እንድናስተውል ይረዳና ል። በቀጣይነት እና በለውጥ መካከል ጭንቅንቆሽ እንደ ነበረም ለመገመት አያዳግ ተንም። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ስናጠና የመጀመሪያይቱ የሐዋርያት ቤተ ክርስ ቲያን በአንድ ቦታ ላይ የረጋች (STATIC) ሳትሆን፣ ብዙ የሚያስገርሙ የለውጥ

ንግግሮች ውስጥ የነበረች (DYNAMIC) ስለ ሆነች፤ በብዙ ጥንቃቄና ማስተዋል እን ድንመለከተው እንገደዳለን:: በአጠቃላይ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የምናያቸው የአገልግ ሎት ስጦታዎችና ቢሮዎች (OFFICES) በሙሉ የተሰጡት የእግዚአብሔር ቤት ሥራ መልክና ሥርዓት ባለው መንገድ እንዲሠራ ለማድረግ ከጌታ የተሰጡ እንጂ፤ (FOR THE SAKE OF FUNCTIONALITY) የሥልጣንና የኃይል ጥያቄን ለመመ ለስ፥ የሥልጣን መውዋቅር ልማሳየት፤ ወይንም መሪው ያለውን ቦታ (STATUS) ለመግለጽ የተሰጡ አይደሉም!!!

1. ሥልጣን በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን፡-
   (የሐዋ. ሥራ 1:4-8፤2:42፤4:34-35፤ 6:1-6)

ጴጥሮስ በኢየሩሳሌም በተጀመረችው የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ብዙ ሚና ሲጫወት እንመለከታለን:: ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እንደገለፀው ጴጥሮስ የሐዋርያትን ቡድን በመወከል ቀዳሚ ተናጋሪ ብቻ ሳይሆን መሪም እንደነበረ እናያ ለን:: በወንጌላትም ላይ ስሙ ከአሥራ ሁለቱ በቅድሚያ ሲጠቀስ፤ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 5 ላይም በሐናንያና በሰጺራ ላይ ፍርድ ሲያስተላልፍ፤ ከዮሐንስ ጋር ሆኖ ም የሽባው እግር እንዲፈወስ ምክኒያት ሲሆንም (የሐዋ. ሥራ 3:1-10)፤ በጥላው እንኳን ሳይቀር ሰዎች እንዲፈወሱ ምክኒያት ሲሆን የምናየው ሐዋርያው ጴጥሮስ እንደሆነ እናያለን:: ይህን ስንመለከት የእግዚአብሔር ጸጋና ክብር አይተን እንድና ደንቅ ያደርገናል:: ከዚህም በላይ ሐዋርያው ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ፤ በውጭ ያለውንም ሕዝብ በተለያዩ ጊዜያት የተናገረው እሱ እንደነበር እናስተውላለን:: (የሐዋ. ሥራ 1:15-27፤ 2:17-41፤ 3:11-26፤ 4:13-33፤ 5:1-11፤ 15:6-11)

በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን ጴጥሮስ የነበረው ሚና "ከእኩዮቹ አንዱ" ("ONE OF THE EQUALS") ነበር እንጂ፤ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እንደሚታመነውና በካሪ ዝማቲክ ሙቭመንት መካከል እየተለመደ እንደመጣው የተለየና ከሌሎቹ በላጭነት ያለው ልዩ "ሥልጣንና ኃይል" የተሰጠው ሰው አልነበረም:: ለምሳሌ ሥላሴዎች በተ ደጋጋሚ ጊዜያት በጴጥሮስ ንግግር መሃል እንኳ ሳይቀር ጣልቃ ሲገቡ እንገነዘባለን :-እግዚአብሔር አብ (ማቴ. 17:5)፤ እግዚአብሔር ወልድ (ማቴ. 16:23)፤ እግዚአ ብሔር መንፈስ ቅዱስም (የሐዋ. ሥራ 10:44):: ጌታ ኢየሱስ ስማቸው እንዲለወጥ ያደረጋቸውና በኋላም ወደ እርሱ እንዲቀርቡ የፈቀደላቸው ጴጥሮስ፥ ያዕቆብና

ዮሐንስ ናቸው:: ምንም እንኳን ስምዖን ይባል የነበረውን ጌታ ኢየሱስ "እኔም እልሃ ለሁ፤ አንተ ጴጥሮስ ነህ፤ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፤ የገሃነም ደጆችም፤ አይችሉትም::" ቢለውም፤ ቤተ ክርስቲያንን የሚያቆምና አጽንቶ የሚይዝ ዓለት ብዙ ድካም የነበረው ጴጥሮስ አይደለም:: ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮ. 10፡4 ላይ "ያም ዓለት ክርስቶስ ነበር::" እንዳለው (ማቴ. 7:24-25) የቤተ ክርስቲያን መሠረትና ዓምድ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው:: በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 10 የቆርነሌዎስ ቤተሰብ ወደ ጌታ ለመምጣትና ለአይሁድና ለአሕዛብ የወንጌል በር ከፋች ሆኖ ብናየውም፤ በአንድ በኩል በምዕራፍ 11:2-3 ከአሕዛብ ጋር በመብላቱ ሲወቀስ፤ በሌላ በኩል ደግሞ አይሁድን ፈርቶ ከአሕዛብ ጋር መብላቱን አቁሞ ሲነሣና በሐዋርያው ጳውሎስ ሲወቀስ (ገላትያ 2:11-14) እናያለን:: ከዚህም በተጨማሪ ለሐዋርያትም ሪፖርት ለማድረግ ተጠያቂነት እንደነበረው ሲገለጽ (የሐዋ. ሥራ 11:1-2) ስናይ ሐዋርያው ጴጥሮስ "ከእኩዮቹ አንዱ" ነበረ የሚለው ሐሳብ የጸና ያደርገዋል:: (የሐዋ. ሥራ 15:1-35)

ስለዚህ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን ስንመለከት የተለያዩ የሥልጣን ሽግግሮች እንደነበሩ፤ ሆኖም ግን በቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ የአመራር ጥሪና ጸጋ የነበራቸው ሰዎች እንደነበሩ እናያለን:: በመጀመሪያ ጴጥሮስና አሥራ አንዱ (አሥራ ሁለቱ) ሐዋርያት ግልጽ የሆነ ሥልጣን፤ ከዚያም በምዕራፍ 15 ሥልጣኑ የጌታ ወንድም የነበረውና በኋላ ጴጥሮስን ተክቶ የኢየሩሳሌምን ቤተ ክርስቲያን ፓስተር የነበረው ያዕቆብ፥ ሐዋርያትና ሽማግሌዎች እጅ ሲሸጋገር፤ በምዕራፍ 21 ደግሞ ያዕቆብና ሽማግሌዎች ሥልጣን ሲለማመዱ ስንመለከት፤ <u>በኢየሩሳሌም ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር መንግሥት እያደገና እየሰፋ በመሄድ ላይ እንጂ፤ "የሥልጣን የኃይል" ጥያቄ ለመመለስና በማን እጅ እንደነበረ ለመግለጽ አልነበረም::</u>

## 2. ሥልጣን በአሕዛብ ቤተ ክርስቲያን፡-

በአሕዛብ መካከል የነበረው የቤተ ክርስቲያን የሥልጣን ጥያቄ ከነበረው ይልቅ የበለጠ ግልፅ አልነበረም:: በእርግጥ በበርናባስና በጳውሎስ፤ በኋላም በጳውሎስ የሥልጣን ልምምድ እንደነበር በመጠኑ ለማየት እንችላለን:: ከበርናባስ ጋር ከተለያዩ በኋላ (የሐዋ. ሥር 15፥36-41) ጳውሎስ የአመራር ቡድን እንዳቋቋመ ለመመልከት እንችላለን:: ለምሳሌ:- ሲላስ፤ ጢሞቴዎስ፤ ቲቶ፤ አፍሮዲጡ፤ ሉቃስ፤ ወዘተ. (የሐዋ. ሥር 15:40፤ 16:3፤ ፊል. 2:20-21፤2ቆሮ. 2:12-13፤ ፊል. 2:25-30) ሐዋርያው

ጳውሎስ ወደ አገልግሎቱ ማጠቃለያ አካባቢ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ን ጠርቶ "በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠ ንቀቁ።" (የሐዋ. ሥራ 20:1-35) ሲላቸው እናያለን። ከዚያም በፊት ጢሞቴዎስንና ቲቶን በተመሠረቱት አብያተ ክርስቲያናት ሽማግሌዎችን እንዲሾሙም ትዕዛዝ ሲሰ ጣቸውና ለሽምግልናና ለዲቁና የሚመርጡአቸው ሰዎች መለኪያ የሚሆናቸውን መለኪያ ሲሰጣቸው እናያለን።

ስለዚህም ከእነዚህ ሐሳቦች በመነሣት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ ያልተጻ ፈውን ሐሳብ ይዞ የሌለውና ያልተባለውን ማንበብ የሚረዳ አይመስለኝም። በአዲስ ኪዳን ያሉት መጻሕፍት የሥልጣን ተዋረድና መዋቅር፤ ሥልጣንና ኃይል በማን እጅ እንደነበር፤ ወይንም ሥልጣን ከሐዋርያትና ከፓስተሮች እጅ ወጥቶ ወደ ሽማ ግሌዎች እንደ ተዛወረ ለማሳየት አይደለም። ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክር ስቲያን ሽማግሌዎች አደራ በሚሰጣቸው ጊዜም ብቸኛ የሆነ ሐሳብ ከመሆኑም ሌላ፤ ዓላማው የሥልጣን ሽግግር እንዳለ ለማሳየት አልነበረም። የሐዋርያት አገልግሎት አብቅቶ፤ ሽማግሌዎች ብቻ የሚመሩት አመራር እንደ ጀመረ ለመግለጽ አልነበረ ም። ምንም ጊዜም ቢሆን መጽሐፍ ቅዱስን እናነባለን እንጂ፤ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ የመሰለንን የራሳችን ሐሳብ አናነብለትም!!! አስቀድሞ የተጠነሰሰ የራሳችንን ሐሳብ ይዘን የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ ያልተናገረውን እንዲልልን ከማስገደድ ልንቆጠ ብ ይገባናል!!!

ስለዚህ ሉቃስ የሐዋርያት ሥራን በሚጽፍበት ጊዜ ሊለው ያልፈለገውን ሐሳብ ለእኛ እንዲልልን ማድረግ አንችልም!!! (WE CANNOT HAVE A MEANING, WHAT IT DID NOT MEAN TO THE ORIGINAL WRITER OF THE BIBLICAL TEXT!!!) የሉቃስ ዓላማ የቤተ ክርስቲያንን ድርጅታዊ መዋቅር ለማ ሳየት አልነበረም።

ከዚህ ይልቅ በአሕዛብ መካከል የነበረችው ቤተ ክርስቲያን አመሠራረቷ፥ ዕድገ ትዋና፥ ፈጣን የሆነ ለውጧን ለመግለጽ ነበር እንጂ። የሐዋርያት ሥራም ይሁን፤ የአዲስ ኪዳን መንፈስ "የሥልጣንና የኃይል ጥያቄ" ለመፍታት፤ ድርጅታዊ መዋቅ ሩን ለማሳየት፤ ወይንም መሪዎቹ በተናጠል ያላቸውን ቦታ ለመግለጽ ሳይሆን፤ እየደ መቀች፥ እያደገችና እየሰፋች የመጣችውን ቤተ ክርስቲያን ምንነትና የዕድገት ለው ጧ ጋር የሚሄድ አመራር እንደሚያስፈልጋት ለማሳየት ነው። ከዚህ የተነሣ ሉቃስ

ም ሆነ ሌሎቹ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊው ቀጣይነት(CONTINUITY) እና ለውጥ (CHANGE) እንዳለ የመልዕክታቸው ቁልፍ ሐሳብ እንደሆነ መገንዘብ ይኖርብና ል:: በፈጣን እድገት የነበረችው የአሕዛብ ቤተ ክርስቲያን የጸጋ ቀጣይነት እና ዕድገ ቱ ራሱ የሚያመጣው ለውጥም የሚታይበት ቤተ ክርስቲያን ነበረች::

***<u>የእግዚአብሔርን ቃል በምናጠናበትና በምንተረጉምበት ጊዜ አራት ዋና ነገሮችን ማሰብ በጣም ወሳኝ ነው:-</u>***

- <u>አንደኛ</u> ስለ እግዚአብሔር ቃል ያለን አመለካከት ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ በጣም አስፈላጊ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብና ስናጠና የእግዚአብሔር ቃል መሆኑንና እግዚአብሔር ሲናገር እኛ ለመስማት እንደሚገባን በማወቅ በፍፁም ፍርሃት፤ መንቀጥቀጥና መገዛት ልንቀርብ ይገባል:: ከዚህም ሌላ የመጽሐፍ ቅዱ ስ ዋና ደራሲው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ በማስተዋል፤ እሱንም ማስተዋላችንን እንዲከፍት በጸሎት መንፈስ መቅረብ አለብን::
- <u>ሁለተኛ</u> የምናነበው የክፍሉ ሐሳብ ሊለው የሚፈልገውን ሐሳብ እንጂ የራሳችን ሐሳብ እንዲልልን ማስገደድ እንደማንችል በመረዳት በጥንቃቄና በማስተዋል ል ናጠናው ይገባል:: የእግዚአብሔርን ቃል ከአግባብ በላይ ለጥጠን መንፍሳዊ ከማ ድረግ ወይም ከማመናፈስ መቆጠብና ሊለው የማይፈልገውን ሐሳብ እንዲልልን ከማድረግ ራሳችንን ልንገዛ ይገባል::
- <u>ሦስተኛ</u> የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍሎች በምናጠናበት ጊዜ በዘመኑ መጀመሪያየተፃ ፈላቸው ሰዎች (የአማኞች ሕብረተ-ሰብ) በፊታችን በማምጣት ለእነሱ ይሰጠው የነበር ትርጉም ልናውቅ ይገባናል:: ለጸሐፊውና ለእነርሱ ያልሰጠው ትርጉም እኛ የተለየ ትርጉም እንደ መሰለን ልንተረጉም አልተሰጠንም::
- <u>አራተኛ</u> እውነተኛ መንፈሳዊነት መጠን በሌለውና አጉል በሆነ ቅንዓት መነሻ በማድረግ የራስን ሐሳብ ይዞ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብና ስውር የሆነ ግትር አምልኮ ሳይሆን፤ እግዚአብሔር በቃሉ ለሚናገረው ነገር ፍፁም የሆነመስጠት፣ መገዛትና፣ መታዘዝ ነው::
- <u>በመጨረሻም እውነተኛና ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጐም የእግዚአብሔ ር ቃል፣ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲተረጉም መፍቀድ ነው</u>!!!

### ሠ. መሪዎችና የእግዚአብሔር ሕዝብ በአዲስ ኪዳን:-

በብሉይና በአዲስ ኪዳን መሃል ቀጣይነት (CONTINUITY) እንዳለ ብናውቅም፤ ለውጥም (DISCONTINUITY) እንዳለ መረዳቱ በጣም አስፈላጊ ነው ብዬ አምናለሁ። ከምናያቸው ቀጣይነት ከሌላቸው ነገሮች አንዱ በእስራኤል ሕዝብ ላይ የበላይነት የነበራቸው ከሕዝቡም ተለይተው የሚታዩ ነገሥታትና ካህናት እንደነበሩስናይ፤ በአዲስ ኪዳን ግን ለውጥ ባለው ሁኔታ ሲከሰት እንመለከታለን። ክርስቶስ ኢየሱስ የበላይና ራስ የሆነበት፤ በእርሱም ምክኒያትና እርሱም ለሕዝቡ ሲል በሰጣቸው የጸጋ ስጦታ የሚያገለግሉ መሪዎችና አገልጋዮች አስነስቶ ሲጠቀም እንመለከታለን። ከዚህም በላይ የክህነት መሥመሩም ከሌዊ ነገድ ወጥቶ በኢየሱስ ክርስቶስ ምክኒያት ወደ ይሁዳ ነገድ ሲዛወር፤ በእርሱም ምክክኒያት እኛ ደግሞ በጌታ አምነው የዳኑ ሁሉ "የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን" እንደሆኑ ልናስተውል እንችላለን። (ዕብ. 7፥ 1-14፤ 1ጴጥ. 2፥ 9-10)

እነዚህ መሪዎችና አገልጋዮች ምንም እንኳን በልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታና ጥሪ የሚያገለግሉ ቢሆኑም፤ ሐዋርያው ጳውሎስ "ጌታ እናንተን ለማነጽ እንጂ እናንተን ለማፍረስ ያይደለ በሰጠው በሥልጣናችን ከፊት ይልቅ ብመካ እንኳ አላፍርም።" (2ቆሮ 10፥8) "ስለዚህ ጌታ ለማፍረስ ያይደለ እንደ ሰጠኝ ሥልጣን..." (2ቆሮ.13፥10) "ስለ እናንተ እንደ ተሰጠኝ እንደ እግዚአብሔር መጋቢነት ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ልፈጽም እንድሰብክ እኔ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሆንሁ።" (ቆላስይስ 1:25) "የእግዚስብሔርን ጸጋ አልጥልም።" (ገላ. 2:21) እንዳለው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማነጽና ለማሳደግ በጌታ የተጠሩ ሰዎች ናቸው። (ኤፌ. 4:11-16) ስለዚህ በአዲስ ኪዳን መሪዎችና አገልጋዮች እንደ ፈሪሳውያን የከበሬታን ወንበር ፈላጊ፤ ለስማቸውና ለስያሜአቸው ተሟጋች፤ ክብርን ከሰው ለማግኘት የሚሳሱ፤ ራሳቸውንም የተለዩ ሰዎች እንደሆኑ የሚቆጥሩ ሳይሆኑ፤ በክርስቶስ አካል ውስጥ የተሰገሰጉ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማገልገል (ለመገልገል ሳይሆን)፤ የተጠሩና ጌታ እግዚአብሔር ከሕዝቡ መሃል በጸጋውና በምሕረቱ ያስነሣቸው ሰዎች ናቸው!!! ሐዋርያው ጳውሎስ "የሆንኩትን የሆንኩ በእግዚአብሔር ጸጋ ነው" ("By the Grace of God, I am what I am!!!") (1ቆሮ. 15፥10) እንዳለው ነው።

**1. የመልዕክቶች ይዘት:-**

የመልዕክቶችን ይዘት ስንመለከት ሁለት ዓይነት ባሕርይ የያዙ መሆናቸውን ለማየት እንችላለን። አንድም ጳውሎስ፥ ጴጥሮስ፥ ዮሐንስና ሌሎችም የጻፏቸው መልዕክቶች የተፃፉት (ካለ ጥቂቶቹ በስተቀር) ለሕዝቡ ነው። ሌላው ደግሞ መሪዎ

ች የተጠቀሱት ጥቂት ቦታ ከመሆኑም ሌላ፣ ቢጠቀሱም ከክርስቶስ አካል ጋር በተያያዘ ነው:: ለብቻቸው የተለየ ቦታ ሲሰጣቸው አናይም:: (1ተሰ. 5÷12-13፣ 1ቆሮ. 16÷16፣ ዕብ. 13÷17) በ1ጴጥሮስ 5:1-4 *መሪዎች* ለብቻቸው የተጠቀሱ ቢመስልም ፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በእረኝነት ሲመሩ ሊያሳዩት የሚገባ ባሕርይ ለመግለጽ ነው:: እንዲያውም በ1ተሰሎንቄ 5:12-13 ሕዝቡ *መሪዎቻቸውን* እንዲያከብሩና እንዲጠነቀቁላቸውም ጥሪ ሲቀርብላቸው እንመለከታለን::[57] እንደዚህ በምንልበት ጊዜ ግን የመሪዎችና የአገልጋዮችን ሚና ለማሳነስና ለማጣጣል አይደለም:: ይልቁንም በእግዚአብሔር ፊት ያላቸው ጥሪ የከበርና የላቀ መሆኑንና፥ የእግዚአብሔር ሕዝቡም አክብሮና ተጠንቅቆ መያዝ እንዳለበት ለመግለጽ ነው!!! በዚያ መጠን መሪዎችና አገልጋዮችም የተሰጣቸው ጥሪና የመሪነት ስፍራ የእግዚአብሔር ቤት እንዴት ይሠራ ቢባል የተሰጣቸው እንጂ፣ የመሪነታቸውን ሥልጣንና ኃይል ለማሳየት የተሰጠ አይደለም::

**2. የአዲስ ኪዳን እይታ:-**

የመልዕክቶችን ይዘት በምናይበት ጊዜ ከጠቅላላ የአዲስ ኪዳን መንፈስ ጋር ይስማማል:: ይኸው ዋናው ትኩረታቸው ግለሰቡ ሳይሆን ሕብረተ-ሰቡ ላይ ነው:: ግለሰቡ ቢጠቀስም እንኳን ከሕብረተ ሰቡ አንፃር/ አኳያ ነው የተጠቀሰው:: ጆን እምቢቲ የተባለው ኬንያዊ የሥነ-መለኮት ምሁር አፍሪካውያን ያለንን ፍልስፍና ሲያጠቃልለው እንዲህ ይላል:- “እኔ የሆንኩት፥ እኛ ስለሆንን ነው፣ እኛ ስለሆንንም እኔ ሆኜአለሁ::” ("I AM, BACAUSE WE ARE; SINCE WE ARE, THEN I AM!"[58] የእግዚአብሔር ሕዝብ አንዱ የሌላው ብልት ነው (ሮሜ 12÷5: ኤፌ. 4÷25)፣ አንዱ ሌላውን ለማነጽ የተጠራ (1ተሰ. 5÷11፣ ሮሜ. 14÷19)፣ አንዱ ሌላውን ለመደገፍ (1ቆሮ. 12÷25)፣ እርስ በርሱ ለመዋደድ (1ተሰ. 3÷12፣4÷9፣ ሮሜ 13÷8)፣ እርስ በርሱም ይቅር ለመባባል (ኤፌ. 4÷32)፣ አንዱ ለሌላው ለመገዛት (ኤፌ. 5÷21)፣ አንዱ ሌላው ከራሱ እንደሚሻል ለማሰብ (ፊል. 2:3) የተጠራ ሕዝብ ነው:: አንዳንድ ጥቅሶች ምንም እንኳን ለግለሰብ የተነገሩ ቢመስልም ( ለምሳሌ:- 1ቆሮ. 3

---

[57] ይኸንን በተመለከተ የበለጠ ለማጥናት የሚከተለውን ማንበብ ይቻላል:- E. Best *The First and Second Epistles to the Thessalonians*, (San Francisco, CA: Harper & Row, 1972), 224-225.

[58] John S. Mbiti, *African Religions and Philosophy,* Heinemann, 1969).

:10-15፤ ፊል. 2:12-13) እነዚህ ሐሳቦች የተነገሩት ለብዙኃኑ ሕዝብ፥ ለክርስቶስ አካል እንጂ ግለሰቡ በተናጠል አይደለም።

ስለዚህ መሪዎችና አገልጋዮች በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ሥልጣናቸውን ለመ ለማመድ የተጠሩ፤ የተጠሩለትንም ሕዝብ አሽቆልቁለው በማየት ተጠቃሚ እንደሆ ነ የሚያስቡ፤ ለራሳቸው በተናጠል የተሰጠ ተጠያቂነት የሌለው "ሥልጣንና ኃይል" ያላቸው ሰዎች አይደሉም። ሐዋርያው ጳውሎስ "ለእናንተ ሲባል የተሰጠኝ የመጋቢ ነት ጸጋ..." እንዳለው ነው። (ቆላ. 1:25) እንዲያውም መሪዎችና አገልጋዮች "...እኛ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ነን፤ እናንተ የእግዚአብሔር እርሻ፤ የእግዚአብ ሔር ሕንፃ ናችሁ።" (1ቆሮ. 3:5-9)፤ "*እንዲሁ ሰው እኛን እንደ ክርስቶስ ሎሌዎች ና እንደ እግዚአብሔር ምሥጢር መጋቢዎች ይቁጠረን።*" (1ቆሮ. 4:1-3) <u>አዲስ ኪዳን መሪዎቹ ያላቸው የሥልጣንና የኃይል እርከን፥ ወይንም የአመራራቸው መዋቅር ለመግለፅ ፍላጎት የለውም። ምክኒያቱም መሪዎችና አገልጋዮች ከጥሪያቸ ው ክቡርነትና ይዘት የተነሳ፥ የጠራቸውን ጌታ የሄደበት የአገልጋይ መሪነት በመከ ተል በፍፁም ትሕትናና የዋህነት ሊመላለሱ ይገባቸዋል!!!</u>

### 3. የሥነ መለኮት መሠረት:-

ከአመራር ጋር በተያያዘ መልኩ አዲስ ኪዳን ከብሉይ ኪዳን ጋር ሙሉ በሙሉ ቀጣይነት እንደሌለው ለማሳየት የሥነ መለኮት መሠረቱ መዳሰሳችን በጣም አስፈላ ጊ ነው። ይህንን ለማየት እንዲያመች ሦስት ዐበይት ጉዳዮችን ለመጥቀስ እወዳለሁ :-የክርስቶስ ሥራ፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታና የወደፊት ተስፋ።

### ❖ የክርስቶስ ሥራ:-

የአዲስ ኪዳን ዋናው ማዕከላዊ እውነት:- "*እግዚአብሔር እርሱን ጌታና ክርስቶ ስ አድርጎታል።*" የሚለው ሐሳብ ነው። (የሐዋ. ሥራ 2:36) ይህ ሐሳብ ሁሉንም ነገ ር ይለውጣል። በአንድ በኩል የተስፋ ሁሉና የመጠባበቅ ቁንጮና ጣሪያ በመሆን ክርስቶስ መምጣቱ አዲስ ከብሉይ ኪዳን ጋር ቀጣይነቱ እና ቀጣይነት የሌለው መሆኑን ይገልፃል። ክርስቶስ ኢየሱስ የአብርሃም ዘርና የተስፋ ወራሽ የሆነና አይሁ ድና አህዛብም በአንድነት የተስፋው ወራሾች እንዲሆኑ ያደረገ ነው።(ገላ. 3:16,29) በተጨማሪም ታላቁ ሊቀ ካህን ሆኖ ስለተገለጠ፤ የካህናት ሁሉ አገልግሎትና ያቀር ቡትም የነበረ መስዋዕት የተሻለና የከበረ ለዘላለም መስዋዕት ሆኖ ራሱን ያቀረበ፤ በአ

ናጢዎች የተጣለ የማዕዘን ራስ ድንጋይ፤ በጠላቶቹም የተገደለ የሕይወት ራስ የሆነ ጌታ ነው:: (1ጴጥ. 2:4-8፤ የሐዋ. ሥራ 3:15) በሌላ በኩል የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የብሉይን ሐሳብ አብቅቶ፤ በአዲስ ኪዳን፥ አዲስ ቃል ኪዳን እንዲጀመር አድርጓል:: (ሮሜ 11፥ 1-36)) "*ሁሉንም በክርስቶስ ለመጠቅለል...*" (ኤፌ. 1፥ 10) እንደ ተባለ አይሁድና አሕዛብ ሁለቱም በንስሃና በእምነት በእግዚአብሔር ጸጋ እንዲድኑና አንድ አዲስ ሕብረተ ሰብ እንደፈጥሩ አድርጓል::

❖ *የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ:-*

*ምንም እንኳን በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ምክኒያት ሕልውናውን ያገኘ ቢሆንም፤ ይህ ሁሉ ሥራ የተሠራው ግን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው:: መንፈስ ቅዱስ የትውልዶች ሁሉ ተስፋና* (የሐዋ. 2:16-21) *የር ስታችንም መያዣ ነው::* (ኤፌ. 1:13-14፥ 2ቆሮ. 1:21-22፤ኤፌ. 1:13፥ 4:30) የእግዚአብሔር ሕዝብ ከሌላው የተለየ እንዲሆን ያደረገውና የዓለም ሞኝነት አድርጎ የቆጠረውን የክርስቶስን መስቀል ጥበብ ለመረዳትና ለማስተዋል ያስቻለው መንፈስ ቅዱስ ነው:: (1ቆሮ. 2:6-16) አይሁድና አሕዛብ አዲሱ ሕብረተ ሰብ እንዲሆን ያደረገው፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዲሆን ያደረገውም እርሱ ነው:: (ገላ. 3:2-5) በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለመጓዝ፥ ለመኖርና ምሪትንም ለማግኘት የተቻለው በእርሱ ነው:: (ገላ. 5:16- 28) አይሁድም ሆነ አሕዛብ የእግዚአብሔርን ፊት እንዲያዩና በፊቱም እንዲገኙ የሚያስችል መንፈስ ቅዱስ ነው:: (ኤፌ. 2:18) አንድ አካል እንዲሆኑም ያደረገው እርሱ ነው:: (1ቆሮ. 3:16-17)

ከዚህም በተጨማሪ በአዲስ ኪዳን ያለን ሰዎች ስለ አመራርና አገልግሎት ያለን አመለካከት እንዲለወጥ አድርጓል:: በብሉይ ኪዳን እንደነበረው መሪነት በግለሰቡ ላይ ያጠነጠነና ከአንድ ነገድ በመሆን የሚገኝ ሳይሆን፤ "*መንፈስም እንደወደደ ለእ ያንዳንዱ እንደ አቅሙ ያካፍለዋል::*" (1ቆሮ 12:11) እንዳለው ሐዋርያው ጳውሎስ የአመራርና የአገልግሎት ስጦታ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው:: እግዚአብሔር መከራን በሕይወታችን እንዲመጣ ሲፈቅድም (1ቆሮ. 10:13)፣ የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታ ሲሰጥ (1ቆሮ. 12:11)፣ ወይንም ትዕዛዝንም ሲሰጥ (ራዕይ 2:24-25) አቅማችንን መጥኖ ነው!!! ከዚህ ሁሉ የምንረዳው በአመራርና በአገልግሎት ላይ በጥሪ የተሾሙ ሰዎችንም ይሁን፥ በክርስቶስ አምኖ የዳነ ምዕመንንም በመንፈስ እንዲሞሉ ማድረግ ብቻ ሳይሆን፤ ኃይልንም በማልበስ ከራሳቸው ያለፈ ሥራ እንዲሠሩና ከተራ ሕይወ

ቅ ያለፈ መለኮታዊ የሆነ ታሪክ ሠርተው እንዲያልፉ የሚያደርገው መንፈስ ቅዱስ ነው::

◆ **የወደፊት ተስፋ:-**

አዲሱ ሕብረተ ሰብ የሆነው የክርስቶስ አካል በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ምክኒያት የወደፊት ተስፋና ርስት ያለው ሆኖአል:: (1ቆሮ. 10::11) ይህ ሕብረተ ሰብ የክርስቶስን መምጣት በተስፋና በናፍቆት የሚጠባበቅ (ፊል. 3:20-21) እና የራሱንም አካል መለወጥና፥ የማይሞትና የማይበሰብስ አዲስ አካል ለብሶ በትንሣኤ መነሣትን የሚጠባበቅ ሕዝብ ነው:: (1ቆሮ. 15:20-28) "***አሁን፥ ነገር ግን ገና***" (*"The Already, and Not Yet!"*) የሚለውን ጭንቅንቆሽ አስታርቆ የሚኖር ሕዝብ ነው:: (1ዮሐ. 3:1-2) "አሁን" ክርስቶስ የሞትን ኃይል አጥፍቶ እንደተነሣ፣ በትንሥኤው ምክኒያት ፈውስ፥ ተአምራት፥ ምልክትና ድንቅ ልንጠብቅ እንደምንችል እናውቃለን:: "ነገር ግን ገና" ጌታ ኢየሱስ በክብር እስኪገለጥና "ይኽ የሚሞተው ሰውነታችን የማይሞተውን ለብሶ፣ ይኽ የሚበሰብሰውም ሰውነት የማይበሰብሰውን ለብሶ እስኪነሣ ድረስ" ፈውሳችን ፍፁምነት ያለው አይደለም:: ምንም እንኳን የወደፊቱ ተስፋችን በአሁኑ ዘመናችን እየኖርነው ቢሆንም፣ ቅምሻ ብቻ እንደሆነ መረዳት ይኖርብናል:: በአንድ በኩል "በሰማያዊ ስፍራ" ከክርስቶስ ጋር የተቀመጥን ብንሆንም፥ በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ ምድር ላይ የምንመላለስ፣ በእግዚኤብሔር መንግሥት የምንመራና የምንገዛ ብንሆንም፥ ለምድራዊ መንግሥትም መገዛት ይኖርብናል:: በእግዚአብሔር ፊት በክርስቶስ ሥራ ምክኒያት ያለን ቦታ "ቅዱሳን" ብንሆንም፥ ነገር ግን ገና ተሠርተን ያላለቅን ስለሆንን "ቅዱሳን ለመሆን የተጠራን ነን::" (ኤፌ. 1:4፣ 4:25-32፣ ሮሜ 13:1-7፣ 1ቆሮ. 1:2፣ ሮሜ 1:7)

ይህንን ሐሳብ ለማጠቃለል ጥቂት ማጠቃለያ ሐሳቦችን መስጠት አስፈላጊ ነው:: በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ምክኒያትና ኢየሱስም ከይሁዳ ነገድ በመምጣቱ የክህነት አገልግሎት ከሌዊ ነገድ ወጥቶ ወደ ይሁዳ ነገድ ተዛውሮአል:: ከዚህ የተንሣ የክህነቱ አገልግሎት መሥመር ስለተለወጠ፣ ሕጉ ደግሞ መለወጥ ነበረበት:: የእግዚአብሔር ጽድቅ በሕግና በሥራ መሆኑ ቀርቶ በጸጋና በእምነት ሆነ:: (ዕብ. 7: 1-28) ታላቁ ሊቀ ካህን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ፣ ከሌዊ ነገድ የአሮን ዝርያ የነበሩት ሊቀ ካህናት በዓመት አንዴ ወደ ቤተ መቅደስ እየገቡ ለራሳቸውና ለሕዝቡ መስዋዕት ማቅረባቸው ቀረ:: ከዚህም ሌላ የካህናትም አገልግሎት ለአንድ ነገድ የተሰጠ ሳይሆን፣ ከነገድ፥ ከቋንቋ፥ ከሕዝብ ሁሉ፥ የተውጣጣው አዲሱ ሕብረተ ሰብ (ማለትም፥

ቤተ ክርስቲያን) "እናንተ የንጉሥ ካህናት ናችሁ..." እንደተባለ (1ጴጥሮስ 2:9) በክርስቶስ አምኖ የዳነ ሁሉ የካህናት ጉባዔ ሆነ።

ስለዚህም መንፈስ ቅዱስ አንዳንዶችን ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት እየለየ፣ እየጠራና እየቀባ፣ ሌሎችን ደግሞ በተሠማሩበት የሥራ መስክ ውስጥ ሆነው የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋት የሚጠቀምባቸው ናቸው። ሁለቱም በጣምራ የእግዚአብሔርን ቤት ሥራ እንዲሠሩ ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታ እየሰጠ የሚያስነሣቸው እርሱ ነው። መንፈስ ቅዱስ ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎችን በሰዎች አፈሰሰ እንጂ፣ የሰዎች አመራር መዋቅር፣ ወይንም የቢሮዎች እርከን አልፈጠረም። በአዲሱ ሕብረተ ሰብ ውስጥ "ነገሥታት" ወይም "የተለዩ ካህናት" ሊኖሩ አይችሉም፣ ምክኒያቱም ይህ መንግሥት በክርስቶስ ሞት÷ ትንሣኤና በመንፈስ ቅዱስ አስደናቂ ሥራ የተጀመረ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥራ ነው። እግዚአብሔር ብቻውን የበላይ የሆነበት÷ የጌታን ጌትነት ማዕከል ያደረገና÷ የመንፈስ ቅዱስም ክብር የሚገለጥበት መንግሥት ነው!!!

4. የአመራር መዋቅርና አገልግሎት በአዲስ ኪዳን:-

በአዲስ ኪዳን ጥናት ውስጥ በጣም አስቸጋሪ ከሆኑ ጥያቄዎች መካከል አንዱ አመራር እንዴት እንደ ተቀረፀና መዋቅሩም ምን እንደነበረ ከሚደረግ አሰሳ ጋር የተያያዘ ነው። በግልፅ የተቀመጠና ሆነ ተብሎ የተሰጠ መመሪያ ባለመኖሩ ችግሩን የበለጠ ያባብሰዋል።

አመራር ሁለት ዓይነት ገጽታ ያለው ነበር። በአንድ በኩል እየተዘዋወሩ የሚያገለግሉ የነበሩ ሐዋርያው ጴጥሮስና ጳውሎስ÷ ሌሎችም የሚታይ የሐዋርያነት ሥልጣን ሲለማመዱ እናያለን። በሌላ በኩል ደግሞ በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ተቀምጠው የሚያገለግሉ "ሽማግሌዎች" እንደነበሩም እንመለከታለን። በብሉይ ኪዳን በተለይም ከምርኮው ዘመን በኃላ በየምኩራቡ ሲያገለግሉ የነበሩት "ሽማግሌዎች" በአዲስ ኪዳን በሐዋርያትና በሌሎች አገልጋዮች ተመርጠው ማገልገል ለጀመሩት "ሽማግሌዎች" ሞዴል ሆነው እንደነበሩ መገምት አያዳግተንም። ሐዋርያው ጳውሎስ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ራሳቸውን "ሐዋርያት" አድርገው ከሾሙና "...*እነርሱ ራሳቸውን ከራሳቸው ጋር ሲያመዛዝኑ ራሳቸውንም ከራሳቸው ጋር ሲያስተያዩ አያስተውሉም።*" (2ቆሮ. 10: 12-18) ከሚላቸው ሰዎች እንዲጠበቁ ሲያስጠነቅቃቸው እናያለን። ከዚህም ሌላ ጳውሎስ ጢሞቴዎስንና ቲኪቆስን በኤፌሶን ቤተ

ክርስቲያን በሐሰት አስተማሪዎች የተፈጠረው አወዛጋቢ ችግር እንዲያስተካክሉ ሊወክላቸው እንመለከታለን:: ይህ ችግር ምናልባትም በዚያች ቤተ ክርስቲያን "ሽማግሌዎች" በነበሩ የተፈጠረ ሳይሆን አይቀርም::[59] ጢሞቴዎስ ጳውሎስን ወክሎ በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን የተዘባረቀ ሁኔታ ከማስተካከልም አልፎ፤ በውድቀት "ሽማግሌዎች" ምትክ ሌሎች "ሽማግሌዎችን" እንደ እግዚአብሔር ቃል መሠረት እንዲመርጥም ያዘዋል::(1ጢሞ. 5፡ 17-22፤ 2ጢሞ. 2፡ 2፤ 4፡ 9) እነዚህ "ሽማግሌ ዎች" ለማስተማርና ለመግር ብቃት ያላቸው ከመሆናቸውም ሌላ ብዙ የተገለጠ ሐሳብ አናይም:: (1ጢሞ. 3፡ 2)

<u>እዚህ ላይ እንድናስተውለው የሚገባን ጉዳይ አመራር በአንድ በኩል በአንድ ግለሰብ ብቻ የሚያጠነጥን ሳይሆን፥ በብዙኃን የሚሠራ መሆኑን፤ በሌላ በኩል ደግሞ የ"ሽማግሌዎች" አገልግሎት መመሥረቱ በሙሉ ጊዜ አገልግሎት የተሰማሩትን በዘመኑ የነበሩ ሐዋርያትን፥ በኋላም የተነሱት ፓስተሮችና፥ ሌሎችም አገልጋዮች አገልግሎት የተካ እንዳልሆነ፤ ይልቁንም ሁለቱ የጣምራ/ የቡድን መንፈስ ኖሮአቸው በመደጋገፍ በአመራር ላይ ሊሰማሩ የሚገባቸው እንደሆኑ ልንገነዘብ ይገባል!!!</u>

◆ **የሐዋርያነት ሥልጣን አድማሱን ማወቅ :-**

የአንድ ሐዋርያ ሥልጣን የሚከሰተው አብያተ ክርስቲያናት በልዩ ልዩ ሥፍራ እንዲመሠረቱና እንዲቋቋሙ በማድረግ የሐዋርያነት ሥልጣኑን ሲለማመድ ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ "...<u>*የእግዚአብሔር አብ ሐዋርያ የሆነ እንጂ፤ ከሰዎች ወይም በሰው ያልሆነ ጳውሎስ*</u>..." (ገላ. 1፡1-2) እንዳለው <u>ሐዋርያት በሰው ወይም በራሳቸው የተሾሙ አይደሉም::</u> ስለዚህ ጥሪያቸው እግዚአብሔር ብቻውን የሚያደርገው መለኮታዊ ጥሪ ነው:: በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ምክኒያት እና በመንፈስ ቅዱስም ኃይል በእጃቸው ፈውስ፥ ተአምራት፤ ድንቅና ምልክት እያደረገ የወንጌልን አዝመራ እንዲዘሩ ጌታ በየሥፍራው እያዞረ ይጠቀምባቸዋል:: ከዚህም በላይ ሐዋርያው ጳውሎስ "*በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንፃችኋል፤ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው::*" (ኤፌ. 2፥20) እንዳለው፤ በሚሰጡት ትምህርትና የትንቢት ቃል <u>መልዕክትና መልዕክተኛ የሆነውን ወንጌል ክርስቶስ ኢየሱስን</u> በማጉላትና

---

[59] የበለጠ ለማንበብ ከተፈለገ የሚከተለውን ማንበብ ይቻላል:- Gordon Fee, *1 and 2 Timothy, Titus- IVP New Testament Commentary Series* by Philip H. Towner, Grant R. Osborne, D. Stuart Briscose and Haddon Robinson, (April 26, 1994).

ማዕከል በማድረግ (ሮሜ 1፡1-4፤ 2ቆሮ. 12፡12) የሚናገሩት ሁሉ የቤተ ክርስቲያን መሠረትና የትውልዶችም መለኪያ ሆኖ ይኖራል፡፡ እንደዚያም ሆኖ በሐዋርያት መካከል የአገልግሎት ጸጋ፥ መከባበር፤ (2ጴጥ. 3፡16-17፤ ገላ. 2፡7-9)፤ ተጠያቂነት (ገላ. 2፡1-2፤11-14)፤ እና የቡድን መንፈስ እንደ ነበራቸው ልናስተውል ይገባል፡፡

❖ *ሥልጣን ሳይሆን፤ የአገልጋይነት መንፈስ ፡-*

ሐዋርያት ከነበራቸው ሥልጣን በስተቀር በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ደረጃ "የሥልጣን ጥያቄ" ለማስተናገድ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ምንም ፍላጎት እንዳልነበ ራቸው እንመለከታለን፡፡ ምንም እንኳን የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪዎቹን እንዲያከ ብርና እንዲገዛላቸው ቢናገርም (1ቆሮ. 16፡16፤ ዕብ. 13፡17፤ 1ተሰ. 5፡12- 13)፤ መሪዎቹ በተናጠል ስላላቸው ሥልጣን ሳይሆን፤ ሕዝቡን ለማነጽና ለመመገብ ስላላ ቸው ትጋትና ስለሚያሳዩትም እንክብካቤ ታይቶ መሆን ይኖርበታል፡፡

**ሬ. ማጠቃለያ ሐሳቦች፡-**

በመጨረሻ እላይ ስናጠናቸው የቆየንባቸውን ሐሳቦች ጥቅለል ባለ መልኩ ስናያ ቸው <u>በአዲስ ኪዳን ውስጥ፤ በተለይም በሐዋርያት ሥራና በመልዕክቶች የቤተ ክርስ ቲያንን አገዛዝ በአጥቢያ ደረጃም ይሁን፥ በጊዜው ከነበረው ዓለም አቀፍ ቤተ ክርስ ቲያን በተመለከተ ግልፅ የሆነ መመሪያ እንዳልነበረ ሊታወቅ ይገባል</u>፡፡ <u>በመጠኑ የአ ሠራር መዋቅር የነበረ ቢመስልም፤ እንደ ሞዴል አድርገን ልንቆጥረው የሚያስችለን ን ያህል ግን አይደለም፡፡</u> አንዱ ምክኒያት የሚሆነው ከመጀመሪያይቱ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን በኋላ የተመሠረቱት አብያተ ክርስትያናት እንደ አንድና አዲስ ሕብረተ ሰብ ራሳቸውን ያዩ ስለ ነበር ግትርና መለውጥ የማይችል የሥልጣን እርከ ን እንዲኖራቸው አለመፈለጋቸው ነው፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር "በሥርዓት ከተለዩ" ("Ordained leaders") መሪዎች ይልቅ፤ "ስጦታ ያላቸው መሪዎች" በመካከላቸው እያስነሳ አስደናቂና ጥልቀት ያለው ሥራ ይሠራ ነበር፡፡

እዚህ ላይ ቆም ብለን ልንጠይቃቸው የሚገቡ ጉዳዮች እንዳሉ መጥቀሱ አስፈላ ጊ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ <u>አንደኛ</u> በእግዚአብሔር ቃል መገለጥ የቤተ ክርስቲያንን አመራርና አሠራር በተመለከተ በግልጽነት በትዕዛዝ የተቀመጠ አይደለም፡፡ <u>ሁለተኛ</u> ስለዚህ በተለያዩ የአዲስ ኪዳን ክፍሎችና ጥቅሶች ውስጥ የታየውን ልምምድ በመቅ ሰም እንዴት አድርገን በዘመናችን ልንሠራበትና ልናገናዝበው እንችላለን? የአዲስ

ኪዳንን ቤተ ክርስቲያን “ሞዴል” ወስደን እንሥራበት ብንል “የትኛው ሞዴል” ውሰድ እንችላለን? ከወሰድንስ ለምን? ሦስተኛ በዘመናችን ያሉት አብያተ ክርስ ቲያናት በተለያየ የእድገት ደረጃና በልዩ ልዩ ባሕሎች መካከል ያሉ በመሆናቸው ልንለማመደው የምንፈልገው የአሠራር ሞዴል በእኛና በሕብረተ ሰባችን ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ ያመጣል? ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ በቀላሉ እናገኛለን ብዬ ማሰብ ልችልም፤ ቆም ብለን አጥልቀን ማሰባችን ግን ይገባል።

በመጀመሪያ ደረጃ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በግልፅ የተቀመጠ የአሠራር መገለጥ እንዳልነበረ በማወቅ እውነታውን ልንቀበል ይገባል። ከዚህ አልፈን ያለ አግባብ ሐሳ ቡን ልንለጥጠው ብንሞክር፤ መጽሐፍ ቅዱስን ከማንበብ ይልቅ፤ የራሳችንን ሐሳብ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እያነበብን ልንለው የምንፈልገውን ሐሳብ እንዲልልን ማስገደ ድ ይሆናል።

በአንድ በኩል የፓስተሮች ቢሮ (Pastoral Office) በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስ ቲያን መኖሩ ከቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አስተዳደር ጋር ተቀናጅቶ እስከሠራ÷ ተጠያቂነት ያለው አገልግሎት እስከሆነ÷ በመሃላቸውም የቡድን መንፈስ እስካልሰፈ ነ ድረስ÷ አክብረን ልንይዘው የሚገባ ጥሩና አገልግሎት ነው። የአንድ ሰው አመራር ሊያስፈራን የሚገባው ትሕትና በጐደለው÷ በትዕቢት መንፈስ፤ ለሥልጣንና ለኃይ ል የሚሳሳና÷ ተጠያቂነት በሌለው ሁኔታ ብቻውን ለማገልገል የሚወድ በሚሆንበት ጊዜ ብቻ መሆን ይኖርበታል!!!

ስለዚህም በሙሉ ጊዜአቸው እንዲያገለግሉ የተጠሩ አገልጋዮች እንዳሉና፤ ቤተ ክርስቲያንን ለማነፅና ለማሳደግ ዘመናቸውን የሰጡ፤ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያ ን ስጦታ እንዲሆኑ የለያቸውና የቀባቸው ሰዎች እንዳሉ ልንውጠው የሚገባ ሐቅ ነው!!! ሆኖም ግን እንዲህ ዓይነት ጥሪ ያላቸው ሰዎችም የተሰጡለት አገልግሎት የክርስቶስን አካል ለማነጽና ለማጎልበት፤ በእግዚአብሔር ሕዝብ ውስጥ ያለውን እም ቅ ስጦታ እየተፈለቀቀ እንዲወጣና እንዲጠቀምበት በመልዕክታቸው÷ በትምህርታ ቸውና በተሰጣቸው የወንጌል አደራ የሚያነሣሱና የሚያበረታቱ ሊሆኑ ይገባቸዋል።

ዋና ዓላማችንና ግባችን “የአመራርና የአሠራር መዋቅር ምንድር ነው?” የሚለ ውን ለመመለስ ሳይሆን፤ የክርስቶስ ዳግም መምጣት እንደሚጠባበቅ አዲስ ሕብረተ ሰብ የአንድነትን መንፈስ በመጠበቅ፤ አንዱ የሌላውን ጸጋ በማክበርና እርስ በርስም መቀባበል ሊሆን የገባዋል። “እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ ደቀ መዛሙርቴ

*እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ።"* **ያለውን የጌታ ቃል** (ዮሐ. 13:34-35) **ለመፈፀም በፍፁም ትሕትናና ቅንነት ልናገለግል ይገባል!!!**

# ምዕራፍ አራት

## መንፈሳዊነትና የአገልጋይነት አመራር

## (Spirituality and Servanthood Leadership)

### *"ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ፥ በልቤም ትሑት ነኝና"*

### (ሉቃስ 22፡27)

በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትም ይሁን፥ ቤተ እምነቶች፥ ወይንም ቤተ ክርስቲያን አገዝ በሆኑ መንፈሳዊ ድርጅቶች የሚያገለግሉ አገልጋዮች በእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን ሥር ተቀምጠው በትሕትና፣ በየዋህነትና በቅንነት ለማገልገል የሚያስችላቸው አንድም በእግዚአብሔር ፊት የሚመዝንና የሚመጥን የነጠረ መፈሳዊነት ሊኖራቸው ነው። ሌላው ደግሞ የአመራር ልምምዳቸውም በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ፊት የአገልጋይነት መንፈስ ሲኖራቸው ነው። ነገር ግን በእነዚህ ሁለት ዓበይት ሐሳቦች የጠራና መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ መረዳት እንደሌለን በአመራራችን ከምናሳያቸው ባሕርያት ማስተዋል እንችላለን። ስለዚህ መጠየቅ ያለብን ጥያቄዎች አሉ። መንፈሳዊነት ምንድነው? "መሪ አገልጋይ" ወይንስ "አገልጋይ መሪ?" የአገልጋይነት አመራር ምንድነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንዲያስችለን መንፈሳዊነትና የአገልጋይነት አመራር እንመለከታለን።

# I. መንፈሳዊነትና አመራር:-

## (Spirituality and Leadership)

### ሀ. የመንፈሳዊነት ትርጉመ ወሰን:-

መንፈሳዊነትና አመራር በተመለከተ ብዙ የተለያዩ ውይይቶች በሥነ ጽሑፉ ዓለም ሲደረግ ቆይቷል::[60] አንዳንድ ጸሐፊዎች "መንፈሳዊነትን" በሰው አነጋገርና ደረጃ ይገልፁታል:: "የውስጠኛው ሰው"፣ "ነፍስ ወይም መንፈስ" ሰዎችን "ወደ እውነተኛ ራሳቸው" እንዲመለሱ የሚያበረታታ የትርጉም አቀራረብ ነው::[61]
ይህ አመለካከት ግን ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ የሆነና እምነትን የሚጻረር ነው::

ሌሎች ጸሐፊዎች ደግሞ "መንፈሳዊነትን" ከሰው ያለፈና፥ ፍጥረታትን የሚያ ካትት ሆኖ "አንድ ኃይል" ("Higher Power") እንዳለና ከዚህም "ከፍ ያለ ኃይል" ሰው ለመኖርና ለመሥራት የሚይስችለው ምንጭ ያገኛል" ብለው ያምናሉ::[62] እን ዲህ ዓይነቱ አመለካከት በእግዚአብሔር ቃል የተመሠረተውን እውነተኛ መንፈሳዊነ ትን የሚቃረን ከመሆኑም ሌላ፣ ከተለያዩ የጥንት ባህሎች የተሰበሰበና ከኒው ኤጅ ሙቭመንት የመነጨ አስተሳሰብ ነው::

በብሉይና በአዲስ ኪዳን የምናየው "መንፈሳዊነት" እውነተኛ መንፈሳዊነት ከመሆኑም በላይ፣ ከመንፈስ ቅዱስ የመነጨ፣ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ጌታ በፍ ፁም ሰብዓዊነቱና በፍፁም መለኮታዊነቱ ማዕከል ያደረገና የእግዚአብሔርን አብ

---

[60] See Jay A. Conger, ed. *Spirit At Work: Discovering the Spirituality in Leadership*, San Francisco, CA: Jossey-Bass, 1994).
[61] See James Hillman, *The Soul's Code: In Search of Character and Calling*, (New York: Random House, 1996); Jack Hawley, *Reawakening the Spirit at Work: The Power of Dharmic Management*, (San Francisco, CA: Jossey-Bass, 1996).
[62] See William C. Miller, *How Do We Put Our Spiritual Values to Work? In New Traditions in Business: Spirit and Leadership in the Twenty First Century*, ed. John Renesch, (San Francisco, CA: Berrett Koehler, 1992), 169-177; Matthew Fox, *The Reinvention of Work: A New Vision for Livelihood for our Time*, (San Francisco, CA: Harper & Row, 1994); Gay Hendricks and Kate Ludeman, *The Corporate Mystic: A Guidebook for isionaries with their Feet on the Ground*, (New York: Bantam Books, 1996); Carol Orsborn, *Inner Excellence: Spiritual Principles of Life Driven Business*, San Rafael, CA: New World Library, 1992).

ክብር የሚያንፀባርቅ፥ በባሕርይ ለውጥ ላይ ያተኰረ የሕይወት እድገት ጉዞ ነው። ከመንፈስ ቅዱስ የመነጨና በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ "መንፈሳዊነት" ብዙ መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖችን የሚያካትት ነው (ለምሳሌ፦ የትህትና፥ የቅድስና፥ የዝምታ፥ ምስጢርን የመጠበቅ፥ የአምልኮ፥ ወዘተ.)። የዲቁናን መንፈስ ሰው በማያ የው መንፈስ የሌሎችን ሰዎች ሕይወት በመልካም ነገር መንካትን/ ማገልገልን ("ዲያኮንያ")፤ በሚያስደንቅ መንገድ የማያዳግም የአዕምሮና የልብ ለውጥና መታደ ስ ማግኘትን ("ሜታኖኢያ")፥ እና ከሌሎች ጋር በቅንነት መንፈስና በልብ አንድነት በመተባበር መኖርንና ማገልገልን ("ኮይኖኒያ") የሚያጠቃልል ሰፊና ጥልቅ ሐሳብና ልምምድ ነው።

## ሰ. መንፈሳዊነት በአመራር ውስጥ ያለው ድርሻ፦

1. መንፈሳዊነት ያለው ሰው ብቻ ነው እያንዳንዱ ሰው የመሰለውን አስተያየ ት ሲሰጥ፥ የእግዚአብሔርን ድምፅ ከሰው ሐሳብ ለይቶ የሚያውቀው።

2. መንፈሳዊነት ያለው ሰው ብቻ ነው ሌሎች በማይመች ሁኔታ ሲሄዱና የኒታንም ሆነ የሰውን ሕግ ሲጥሱ፤ እርሱ ግን የዋጋ እሴቶችን አውቆና አስተውሎ ግመቻመች የማይችለው።

3. መንፈሳዊነት ያለው ሰው ብቻ ነው ሁሉን ነገር መሆንም ይሁን ማድረግ እንደማይችል አውቆ፤ እግዚአብሔር የሰጠውን ራዕይ ለመፈፀም የሌሎችንም የጸጋ ሥጦታዎች የሚጠቀመውና የትኩረት አቅጣጫ ያለው አገልግሎት የሚያገለግለው።

4. መንፈሳዊነት ያለው ሰው ብቻ ነው ከአገልግሎቱም በላይ ሰዎች አስፈላጊ እንደሆኑ አውቆ የግንኙነት ሥምረትን አጥብቆ የሚጠብቀው።

በአመራር ላይ የተቀመጡ አገልጋዮች ዘላቂነት ያለውና ለትውልድ ሊተላለፍ የሚችል ቅርስ እንዲኖራቸው ከፈለጉ የሚከተሉትን ቁልፍ ነገሮች ማሰባቸው በጣም አስፈላጊ ነው ብዬ አምናለሁ።

- ለእግዚአብሔርና ለሰው የሚመችና የሚጠቅም አገልጋይ ለመሆን ከእነርሱ በፊ ት የተሠራው የጌታን ሥራ ማሰብና ማክበርን፤
- ወደፊት ለመዘርጋት፥ ከቀደሙት የእግዚአብሔር ሰዎች ጋር መቆራኘትን፤
- ብዙ ሰዎችን ለማገልገል ከፈለጉ፥ለብቻቸው የሚሆኑበትን ጊዜ ማዘጋጀትን፤
- በጌታ ሥራ ለመትጋት ከፈለጉ፥ በማስተዋል መርጋትን፤

- ብዙ አገልግሎት ለማገልገል፥ የእረፍት ጊዜያት መውሰድና ለሱባዔ መውጣትን
- አንድ ሐሳብ ለመናገር፥ በዝምታና በፀጥታ አስቀደሞ ለመስማት መቻልን፤ (ያዕቆብ 1፡19)
- በእግዚአብሔር ሥራ ለመሮጥ ከፈለጉ፥ የህይወታቸውንና የአገልግሎታቸውን መልህቅ በሆነው በክርስቶስ መመሥረታቸውን መገንዘብና ማረጋገጥ፤
- በአሁኑ የአገልግሎታቸው ዘመን ፍሬአማ ለመሆን ከፈለጉ፥ ዘላለማዊ የሆነ የክብር ተስፋና ብድራት እንዳለ ትኩር ብሎ ማሰብን።

## ሐ. መንፈሳዊ ዲሲፕልኖች፡-

## (Spiritual Disciplines)

መንፈሳዊ ዲሲፕልኖች ብዙ ህብር ያላቸው ናቸው። የጌታን ጌትነት ማዕከል ያደረገ ሕይወትና አገልግሎት እንዲኖረን በማድረግ የእግዚአብሔርን ክብር አንፀባ ርቀን እንድናልፍ የሚረዱ የሕይወት እውነቶችና ልምምዶች ናቸው። እነዚህን መን ፈሳዊ ዲሲፕልኖች በምናይበት ጊዜ መሪዎች የሆንን ሁላችንም ሰዎች በመሆናችን <u>ተሠርተን ያላለቅን ስለሆንን እውነታውን በመቀበል</u> በፍጹም ቅንነት ራሳችን (ሕይ ወታችንም ሆነ አገልግሎታችን) መገምገም ይገባናል። መለወጥ በሚገባን ዲሲፕልኖ ች ላይም በራሳችን መጨከንና የድርጊት ፕላን በማውጣት እርምጃ መውሰድ እንድ ንችል በክርስቶስ ፍቅር አበረታታለሁ።

### 1. የትሕትና ዲሲፕልን፡-

### (THE DISCIPLINE OF HUMILITY)

እኛ ኢትዮጵያውያን ያለን ባህል በክርስትና የተለወሰ ስለሆነ ክርስትናውን ከዓ ለማዊ አስተሳሰብ ጋር አዳቅለን የያዝናቸው ብዙ ነገሮች እንዳሉ እናውቃለን። ከእነ ዚህም መካከል ስለ ትሕትና/ የዋህነት ያለን መረዳት ነው። ከዚህም ሌላ ራሳችን በራሳችን ዓይን እይታ “እንደ እኛ የመሰለ ትሁት ሰው” ያለ አይመስለንም። እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ግን በእግዚአብሔር ቃል ፊት ሊፈተንና ሊስተካከል ይገባዋል ብዬ አምናለሁ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ 11:29 ላይ "*ከእኔ ተማሩ፤ እኔ የዋህ፤ በልቤም ትሑት ነኝና፤*" ብሎ የተናገረው መሠረታዊ ቃል ነው:: እዚህ ላይ ሊጠቀሱ የሚገባቸው ጌታ የገለፃቸው ሁለት ዕረፍቶች አሉ:: የመጀመሪያው "እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም አሳርፋችኋለሁ::" ያለው ቃል ነው:: ይህ ዕረፍት እግዚአብሔር በምሕረቱና በጸጋው በክርስቶስ አምነው ለቀረቡት የሚሰጠው ነው:: ሁለተኛው "ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ፤... ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ::" የሚለው ቃል ነው:: ይህ ዕረፍት ግን የእኛ ባሕርይ ሲለውጥና ጌታን በትሕትናውና በየዋህነቱ ስንመስለው ብቻ የሚገኝ የአገልግሎት ዕረፍት ነው:: አገልግሎት እየከበደ፤ ሸክም እየሆነ፤ እየተሳከረና እየተወሳሰበ የሚመጣው በአገልጋዮች ልብ ውስጥ ትሕትናና የዋህነት ደብዛው እየጠፋ ሲመጣ ነው::

እዚህ ላይ ልንጠይቀው የሚገባን ጥያቄ "ትሕትናና የዋህነት" ምን ማለት ነው? ትሕትና/ የዋህነት ከትዕቢት ጋር ያለው ንፅፅር ምንድነው? እውነተኛ ትሕትና ከውሸት ትሕትና በምን እንለየዋለን? ትሕትና በውጫዊ መግለጫ ብቻ የሚገለጥ ነው ወይንስ የውስጥ ጥራት የትሕትናችን ፍሬ የክርስቶስን ባሕርይ ያንፀባርቃል ወይ? የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ ይገልጻል? በዚህ ውስጥ የከበረው ምንድነው? እኛ ወይስ እግዚአብሔር? (ቆላ. 2:16-23)

*የእግዚአብሔር ቃል ስለ ትሕትናና የዋህነት በአዲስ ኪዳን ውስጥ በግሪኩ ቃል የተሰጠው ትርጉም እንደሚከተለው አስቀምጦታል:-*

- "*ከሚገባ በላይ ስለ ራስ አስፈላጊነት ለማሰብና ለማድነቅ ፈፅሞ አለመፈለግ::*"
- "*የራስን መብት ለሌላው ሰው ጥቅም ሲባል መስዋዕት ለማድረግ ከልብ በመነጨ ሁኔታ ፈቃደኛ መሆን::*"[63]

"ትሕትና/ የዋህነት" (በግሪኩ ቃል "ፕራኡቴስ") "Gentleness, Humility, Considerateness, Meekness") ማለት "መርጋት÷ ትህትና÷ ስለ ሌላው ሰው ማሰብ÷ የዋህነት"[64] ብሎ ይገልፀዋል:: "ትሕትና/ የዋህነት" የኢየሱስን ባሕርይ የሚገልፅ ከመሆኑም ሌላ፤ የነበረው አመራር ምንም ዓይነት ኃይል ሳይጠቀም በምድር ላይ ደህንነት የሚያመጣ ጌታ እንደ ነበረም ያሳያል::(ማቴ. 11:29፤21:5፤ 5:5፤ ዘካ. 9:

---

[63] Colin Brown, ed. *NIDNTT,* vol. 2, 256-264; johannes P. Louw and Eugene A. Nida, eds. *Greek-English Lexicon of the New Testament Based on Sematic Domains*, 2nd. ed., vol. 1 *Introdiction and Domains*, (New York: United Bible Societies, 1988, 1989), 748.

[64] Colin Brown, *NIDNTT,* 256.

9) "ትሕትና/ የዋህነት" በሰው ብቻ የተመረኰዘና በሰው ፈቃድ ብቻ ላይ የተመሠረተ መልካም ባሕርይ ሳይሆን፣ ሰው ጌታ ኢየሱስን በማወቅ እያደገና እርሱንም እየመሰለ ሲሄድ በውስጡ የሚመጣ የሕይወት ለውጥ ነው:: በሰው ዓይን የበታችነትን የሚያመለክትና የሚያሳፍር ነገር ሆኖ ሲወሰድ ስናየው፣ በአዲስ ኪዳን ግን እግዚአብሔርን ማዕከል ያደረገና ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ የሆነ ግንኙነት እንዲኖረው የሚያደርግ የሕይወት ለውጥ ነው::[65] ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የትሕትናን ውበት የገለጸው:-

- ➢ የሥልጣን እርከን የሚፈልጉትን ሲያስጠነቅቅም ይሁን " (ሉቃስ 14:11፣ ማር. 10:15፣ ማቴ 18:4)፣
- ➢ ከፈሪሳውያን ጋር በነበረው የሚያነጋግሩ ጉዳዮች ላይም ያሳየው ትሕትና (ሉቃስ 18:14)፣ እና
- ➢ በፈሪሳውያንና በጸሐፍት ላይ የገለፀው ተግሣፅም፣ እና በትሕትና ለሚመላለስ ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚሰጠው ብድራትና ተስፋም (ማቴ. 23:12 ) እንዳለ በገለጸበት ጊዜ ነው::

ዊልያም ቴምፕል የሚባለው የእንግሊካን ቤተ ክርስቲያን አርክ ቢሾፕ አፍ ካን ተበሪ ሆኖ ያገለገለው ሰው (እ.አ.ዘ.አ 1942-1944 ዓ.ም) ስለ "ትሕትና/ የዋህነት" እንዲህ ብሎ ተናግሮ ነበር:- "ትሕትና ማለት ራስን ከሌሎች አሳንሶ ማየት፣ ወይም ስለ ራስ ስጦታ የበታች/ ዝቅተኛ አድርጎ ማየት አይደለም:: እንዲያውም ስለ ራስ ከማሰብ ፈፅሞ ነፃ መውጣት ነው::"[66] "ትሕትና/ የዋህነት ማለት እግዚአብሔር የሰጠን ስጦታዎች፣ ወይም በረከቶች፣ ምህረትና ሞገስ መካድ አይደለም!!! ነገር ግን የሰዎች ዓይን እግዚአብሔር በምሕረቱና በጸጋው ወደ ሰጠን መልካም ነገሮች እንዲሳብ በማድረግ የተለየ ጥቅም፥ ዝናና፥ ክብር ለእኛ እንዲሰጡን በሰዎችልብ ውስጥ ለመሥረጽና ቦታ ለማግኘት ምንም/ አንዳች ጥረት አለማድረግን ይጠይቃል::

- ❖ "ትሕትና/ የዋህነት" ለመረዳት የሚያስቸግር እንግዳ ነገር ነው ምክኒያቱም ያገኘነው በመሰለን ጊዜ ከእጃችን ያመልጣል፣ ደርሰንበታል ስንል ከእኛ እጅግ የራቀ ነው:: ትሁት እንደሆነ ከሚያስብ ሰው በላይ ትዕቢተኛ የለም!!! በአመራር ላይ የተቀመጡ አገልጋዮች ሁሉ ሐዋርያው ጳውሎስ ያለውን ሐሳብ በማስተዋ

[65] Ibid., 260.
[66] see www.lifeondoverbeach.wordpress.com/2011/11/05/William-Temple-about-humility. (accessed June 27, 2013).

ል ሊያጤኑ ይገባቸዋል:- *"አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን ፍፁም እንደሆንሁ አ ይደለም፤ ነገር ግን ስለ እርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ የተያዝሁበትን ያን ደግሞ እይ ዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ:: ....ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውንለመያዝ እዘረጋለሁ::"* (ፊል. 3:12-13)

- "ትሕትና/ የዋህነት" እግዚአብሔርን ማዕከል ያደረገ ሆኖ፤ የእግዚአብሔርን ክብር፤ ኃይልና ለእኛም ሆነ ለሕዝቡ ያለውን ዓላማ ትክክለኛ እይታ እንዲኖረን የሚያደርግ የሕይወት ዲሲፕሊን ነው::
- "ትሕትና/ የዋህነት" በእግዚአብሔር ቃል የተመሠረተና ከመንፈስ ቅዱስ የመ ነጨው፥ ጌታ የሰጠን ሥልጣን ለራሳችን መጠቀሚያ ሳይሆን፤ የምናገለግለውን ሕዝብ ለማሳደግ፤ ለማጎልበትና በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ያለውን ድ ርሻ አውቆ የተሰጠውን መክሊት እንዲጠቀምበት ለማበረታታት ነው::

## (ሀ) እውነተኛ ትሕትና ከአጉል ትሕትናና ከትዕቢት ጋር ሲነፃፀር

| አጉል ትሕትና | ትዕቢት | እውነተኛ ትሕትና |
|---|---|---|
| ራስን ዝቅተኛና ምስኪን አድርጎ ማሰብ | ከንቱና ጊዜያዊ የራስ ክብር በመፈለግ የበላይ እንደሆኑ፤ ማሰብ፤በራስ ሐሳብ መድረቅ፤ | ከልብ የመነጨ ቅንነት የሌላ ው ሰው ጥቅም መፈለግ፤ ከመገልገል ይልቅ ማገልገል፤ |
| የተበላሸ የራስ አመለካከት መያዝ፥ በራስ ላይ አሉታዊ ና አለአግባብ መፍረድ፤ እንደማይረቡ ማሰብ፤ በራስ ማቁዘምዝም:: | ራስን ከሌሎች አስበልጦ ማሰብ፤ በጣም የተለጠጠ የራስ አስተያየት ላይ መጠመድ:: | ለራስ ምንም ሳይሳሱ ሌሎች ን በመስዋዕትነትና በመሰጠ ት ማገልገል፤ ሌሎች ሰዎች ያላቸው አስተያየት አለመፍ ራት፤ ስለ ራስ ከማሰብ ነፃ መሆን:: |
| በሌሎች ፊት ራስን ከመጠ ን በላይ መውቀስ፤ ከሚገባ ና አጉል በሆነ መንገድ ጨዋ ለመሆን መሞከር ም ንም ጥቅምና ረብ የሌለው ሰው አድርጎ ራስን ማየት:: | የራስን ከንቱ ውዳሴ ማብዛት ፤ ስለራስ ብዙ መናገርና መመካት፤ በራስ ችሎታ እው ቀት ልምምድና ስጦታ በሌሎች ፊት መመካት:: | የራስን ብርታትና ድካም ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መረ ዳት፤ ሁሉን ነገር ማድረግና መሆን እንደማይችሉ አውቆ የሌሎችን ፀጋ ማክበር:: |
| ሰውን ሁሉ ደስ ለማሰኘት /ለማርካት መሞከር፤ ትክክ ለኛ የሆነውን ነገር ከማድረ ግ ይልቅ፤ ሰዎች የፈለጉት ን ለመፈፀም መታገል:: | የግል አጀንዳና ፍላጎት ለመ ፈፀም መትጋት፤ የሌሎችን ስ ሜት ደግምጠም ይሁን ከእነ ርሱ በልጦ ለመገኘት መታገ ል:: | እያንዳንዱን ሰው በአክብሮ ት መቀበልና ማገልገል፤ ማ ንም ሰው ያለው ቦታ ሳይገ ደው አድልዎ በሌለው ሁኔ ታ ሁሉንም እኩል ማገልገል |
| በራስ ማቁዘምዘም መዋጥ፥ ስለራስ ብዙ መጨነቅና መታወክ፤ በሌሎች ላይ ለማተኮር አለመቻል:: | "ከእኔ÷በእኔ÷ለእኔ" ራስ ተኮር፤ የራስን ጥቅም ማስጠበቅ፤ ራስን ማምለክ | ራስን በመስዋዕትነት ለሌሎ ች አሳልፎ መስጠት፤ ሌሎ ችን ለመርዳት፥ ለማበረታ ታት፤ ለማገልገል በፍፁም |

| | | |
|---|---|---|
| | | ልብ መስጠት:: |
| ዓይነ አፋር፣ ፈሪ፣ እርግ ጠኝነት የሌለው፣ በራስ አነሳሽነት እርምጃ መው ሰድ የማይችል፣ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ በእርግጠኝነት መናገር የማይችል:: | ሌሎችን ዝቅ አርጎ የሚያይ፣ የማይገባውን ፈላጊ ሌሎችን እንደፈለገ ለመጠምዘዝ የሚ ፈልግ ግምታዊ አስተያየቶች መናገር፣ የሚያበዛ፣ ከመጠን ያለፈ ተናጋሪ፣ የተለጠጠ እርግጠኝነት ያለው ንግግር የሚያበዛ | ሌሎች ተኮር፣ ለሌሎች ቅድሚያ መስጠቱ ብቻ ሳይሆን እነርሱንም የሚ ያሳስባቸው ጉዳይ መሟላቱ ን የሚፈልግ፣ የራሱን ጥቅ ም ሌሎችን ለማገል ሲል መስዋዕት የሚያደርግ:: |
| በሌሎች ሰዎች አስተ ያየት የሚደገፍ ያለነሱ አስተያየትም በራሱ መቆም የማይችል:: | ሌሎች ሰዎች ሁሉ ከእርሱ በታች እንደሆኑ የሚያስብ፣ ሌሎች የሚቆረቁራቸውን ለመረዳት አለመፈለጉ ብቻ ሳይሆን፣ መረዳትም እንደሌ ላቸው የሚያስብ፣ የሚያገለ ግላቸው የተጠራለትን ሕዝብ የሚያማ:: | የአገልጋይነት መንፈስና ልብ ያለው፣ ለራሱ ጥቅም÷ ከእነርሱ የሚያገኘውን ሳያስ ብ የተጠራለትን ሕዝብ በቅ ንነት የሚያገለግል:: |
| ለመታረም የሚፈራ፣ ሲገሰፅ የሚደነግጥ፣ የራሱን መልክ በተበላሸ ሁኔታ ስለሚያይ ሌሎች የሚሰጡትን አስተያየት የማይወድ | መማር የማይፈልግ የተዘጋ ልብ ያለው፣ እርማትም ይሁ ን ተግሳፅ ፈፅሞ መቀበል የማ ይፈልግ፣ የሌሎችን ሐሳብ የሚያጣጥል የሚንቅ | ለመማር ትሁት የሆነ ልብ ያለው ለመታረም ክፍት የሆነ፣ ራሱን እንደበቃ አድ ርጎ ስለሚያይ ለማደግ ውስ ጣዊ ረሃብ ያለው፣ ሌሎች የሚሰጡትን ሓሳብና አስተ ያየት በቁም ነገር የሚወስድ |

## (ለ) እውነተኛ ትሕትና ከትዕቢት ጋር ሲነፃፀር፡-

| እውነተኛ ትሕትና | ትዕቢት |
|---|---|
| ማቴ. 11፡29÷ ፊል. 2፡1-11፣ ዮሐ. 13፡4-7 ማር. 9፡35፣ ዮሐ. 3፡29-30፣ የሐዋ ሥራ 13፡22-23፣36፣ ምሳሌ 18፡16፣ 21፡3፣20፣22 ፡4፣24፡3-4 | ምሳሌ 25፡14፣ 27-28፣ 27፡2፣14፣21፣ ማቴ. 20፡20-28፣ ማር 9፡33-34 |
| ትሕትና ኃላፊነት ይቀበላል:: | ትዕቢት ግን ኃላፊነትን ከመቀበል ይልቅ ሌሎችን መውቀስ ይቀለዋል:: |
| ትሕትና ግልፅ የሆነ ዓላማ አለው:: | ትዕቢት ግን መሸፋፈን÷ ምሥጢራዊ ማድረ ግና መካድ ይወዳል:: |
| ትሕትና ለማስተማር ብቻ ሳይሆን ለመማር አጥብቆ ይፈልጋል:: | ትዕቢት ግን ከተከፈተ አዕምሮ ይልቅ የተደ ፈነ÷ ለመቀበል/ ለመማር ከመፈለግ ይልቅ የተዘጋና ተሟጋች ነው:: |
| ትሕትና ባለበት ሰዎች ያላቸውን ፀጋ በማነሣ ሣት አዲስ ፈጠራዎችን ይለማመዳሉ፣ የእግ ዚአብሔር መንግሥት ያሰፋሉ:: | ትዕቢት ባለበት ስፍራ ግን የሰዎች ሁሉ ፀጋ የታሰረ ነው::፣ እንዲያውም በእግዚአብሔር ቤት ተመልካቾች ይሆናሉ:: |
| ትሕትና መለወጥ በሚችሉና እውነትን በማ | ትዕቢት ግን ለመለውጥ ፈቃደኛ ከመሆን |

| | |
|---|---|
| ይቃረኑ ሁኔታዎችና ውሳኔዎች ላይ ለመለወ ጥ ፈቃደኛ ነው:: | ይልቅ ግትርነት ይመርጣል:: |
| ትሕትና የቡድን መንፈስ ይፈጥራል፣ ሰዎችም በአንድ ልብ ሆነው ለማገልገል ይቀ ናቸዋል:: | ትዕቢት ግን የሰው ልብ እንዲበታተንና እር ስ በርሱም እንዳይተማመን ያደርጋል:: |
| ትሕትና ሰዎች ያለ ምንም ጫና በፈቃደኝነ ት ለተሰጣቸው ነገር ታዛዥ ሆነው እንዲያገ ለግሉ ያደርጋቸዋል:: | ትዕቢት ግን ሰዎች በእግዚአብሔር ሥራ እንዲለግሙና አልፈውም እንዲያምፁ ያደር ጋቸዋል:: |
| ትሕትና ባለበት የጠራ፥የከበረ፣ የላቅና የጠለ ቀ ሥራና አገልግሎት ይካሄዳል:: | ትዕቢት ባለበት ግን የግብር ይውጣና መደረ ግ ስላለበት ብቻ ይደረጋል፣ ህይወት የሌለው ና ህይወት ማመንጨት የማይችል ይካሄዳል |
| ትሕትና የግንኙነት ሥምረትን አስፈላጊነት ስለሚረዳ፣ሰውን ሁሉ እንደየ ክርስትና ዕድገቱ በአክብሮት የሚመራበት ፀጋና ጥበብ አለው:: | ትዕቢት ግን መሪውን ብቸኛ ከማድረጉም በላይ፣ ወደ ሰዎች መቅረብ የማይወድ፣ የሰ ው ሐዘን የማይገባው ግለሰቦችም ሆኑ ሕዝቡ ከመድረክ ብቻ የሚያውቁት እንዲሆን ያደ ርገዋል:: |
| ትሕትና ከምንም ነገር በላይ የእግዚአብሔር ን ፊት ለማየት እንድንናፍቅ ያደርጋል:: (መዝ. 27:4፣8) | ትዕቢት ግን ኃይልና ሥልጣን ፈላጊ እንድን ሆን ስለሚያደርገን ሹመት ፈላጊ እንሆናለን |
| ትሕትና ኑሮአችንም ሆነ አገልግሎታችን በ ፍቅር የተለወሰ እንዲሆን ያደርገዋል:: (1ቆሮ. 13:4-7) | ትዕቢት ግን በውድድርና በፉክክር መንፈስ እንድጠመድ ስለሚያደርገን ዘመናችንን በ ሙሉ ከሌሎች አገልጋዮች ጋር ስንገፋፋ እን ኖር ያደርገናል |
| ትሕትና ከአገልግሎት ስኬታማነት ይልቅ ለእግዚአብሔርና ለሕዝቡ ታማኝነት ላይ እንድናተኩር ያደርጋል::(ማቴ. 25:21፣23) | ትዕቢት ግን በኑሮ ስኬታማነት ላይ እንድና ተኩር ስለሚያደርገን በስስት ባሕር ውስጥ እንድንዋኝ ያደርገናል:: |

- ◆ **ትሕትናን ለመላበስ በእግዚአብሔር ሥራ የተጠመዱ መሪዎች ሁሉ:-**

- ምንም ነገር እንደማያውቁ ሆነው የእግዚአብሔርን ጥበብ፣ (ያዕቆብ 1:5-8)
- ኃይል እንደሌላቸው አውቀው የመንፈስ ቅዱስን ኃይል፣
- ምንም እንዳልሆኑ አስተውለው በእግዚአብሔር ፊት መደፋትን፣
- ያለ እግዚአብሔር ምንም ሊያደርጉ እንደማይችሉ ተረድተው፣ የእግዚአብሔርን ጸጋና ምህረት እንዲበዛላቸው መጠየቅን፣
- ከእጁ ይልቅ ፊቱን በመፈለግ፣ ራሳቸውን በቅንነት ሊያቀርቡ ይገባቸዋል!!!

## ሐ.ትሕትናን ለማግኘት የሚረዱ መንገዶች:-

- ✓ በየጊዜው እውነተኝነት በተሞላበት ሁኔታና በቅንነት ኃጢአታችንንና ስንፍናችንን በፊቱ መናዘዝ:: (መዝ. 51:1-4፣ 139:23-24፣ ሉቃስ 18:9-14፣ ዕብ. 12፡ 1-3)

- ✓ አንዱ የትሕትና መለኪያው በእግዚአብሔር ፊት ያሳየነውን ስንፍናና ኃጢአት በምንወዳቸው ሰዎች ፊትም መግለፅ፣ -ያዕቆብ 3:2፣ 5:16-18
- ✓ የሌሎችን ሰዎች ስህተት ስናይ መታገስ (1ጴጥ. 3:8-17) ሰዎች በእኛ ላይ ሐሜት፣ ወሬና ክፉ ሲናገሩ በትዕግሥት መሸከም፣
- ✓ እግዚአብሔር ላስቀመጣቸው መሪዎችና አገልጋዮችም ይሁን (ዕብ. 13:17፣ 1ተሰ. 5:12-13)፣ ለአገር ባለ ሥልጣናትም (1ጢሞ. 2:1-4፣ ሮሜ. 13:1-7) መታዘዝና መገዛት፣
- ✓ ሰዎች ለሚሰጡት እርማትና ተግሣፅ ፀጋ በሞላበት ሁኔታ መቀበል፣ (ምሳሌ 10:17፣12:1)
- ✓ ሌሎች ከእኛ እንደሚሻሉ መቁጠርና ፀጋቸውንም መጠቀም፣ (ፊል. 2:1-11)
- ✓ ዓላማ ባለው መንገድ በድህነት ውስጥ ካሉት፣ ከተገፉትና በችግር ውስጥ ከተቀመጡ ት ሰዎች ጋር ራስን ማመሳሰል፣ እግራችንን በጫማቸው ውስጥ አስገብተን የችግራ ቸውን አድማስ መረዳት፣
- ✓ በሰው ኃዘን ብቻ ሳይሆን በሰው ደስታ ውስጥም ለመግባትና አብረናቸው ደስ ለመሰ ኘት የምንችልበት መንፈሳዊ ብስለት መያዝ፣
- ✓ የሌሎች መሪዎችና አገልጋዮች ምሥክርነት እንዳይበላሽ ጸጋቸውን መጠበቅ፣ ስለ እነርሱ መልካም ካልሆነ በስተቀር ክፉ ነገር በሌሎች ፊት ወይንም በመድረክ ላይ ከመናገር መቆጠብ፣
- ✓ በየጊዜው እየተለጠጠ ከሚሄድ የትዕቢት መርዝ ራስን መጠበቅ፥ የውስጥ ልብንና መንፈስን መመርመር፥ ራስን በእግዚአብሔር ፊት ማዋረድ፣ (1ጴጥ. 5፥6-7፣ 4፥ 10-11፣ 5፥5)
- ✓ በሌሎች መሪዎችና አገልጋዮች ሥር ተቀምጦ ለመገልገል መፈለግ፥ አመራራቸውን ም ማክበር፥ የእግዚአብሔርንም ጸጋ አይተን በአድናቆት ደስ መሰኘት፣
- ✓ እግዚአብሔር ከደህንነታችን ጀምሮ በሕይወታችን ዘመን ያደረገልንን ውለታ አስበ ን ማመስገን፥ አዲስ ቀን በመጣ ቁጥር አዲስ ምዕራፍ እንደተሰጠን አውቀን በአድና ቆት መቀበል፥ በሕይወታችን ምዕራፎች የምናየውን የእግዚአብሔርን ፊርማ አስበን ማመስገን፥ ጌታ ከየት እንዳነሣን ሁልጊዜ እያሰብን እርሱን በፍጹም ልብ ማክበር::

*"ትሕትናና እግዚአብሔርን መፍራት ባለጠግነት፥ ክብር፥ ሕይወትም ነው::"*
(ምሳሌ 22፥ 4)

## 2. በመጠን የመኖር ዲሲፕሊን፡-

### (THE DISCIPLINE OF SIMPLICITY)

2.1 በመጠን የመኖር ዲሲፕሊን ነፃነት ነው፤ ውስብስብ የሆነ ኑሮ መኖር ግን እሥራት ነው:: ያልተወሳሰበ ኑሮ ደስታንና በመጠን መኖርን እንድንለማመድ ሲያደርግ፥ ውስብስብ የሆነ ኑሮ ግን ጭንቀትንና ፍርሃትን ይፈጥራል:: የእግዚአብሔር ቃል፡- *"እግዚአብሔር ሰዎችን ቅኖች አድርጎ እንደሰራቸው ይህን ብቻ አገኘሁ፤ እነርሱ ግን ብዙ ብልሃትን ፈለጉ::"* (መክብብ 7፥29) በአሁኑ ዘመን የመሪዎችንና የአገልጋዮችን ጸጋ አንቆ የያዘው ጉዳይ በጊዜ መወጠርና ውስብስብ ኑሮ ነው:: እነዚህ ጉዳዮች ሰበባቸው ሳይታወቅ በቀላሉ የተወሰዱ ሆነዋል:: ይህ የዘመናችን "የጥድፊያ በሽታ" የሰውን ሁሉ ሕይወት ያሳከረ፥ ጊዜን ለማግኘት ሲባል የሚደረግ ትግልና ፍሬ አልባ የሚያደርግ ችግር ነው:: በጥድፊያና ውስብስብ በሆነ ኑሮ የሚኖሩ ሰዎች ምንም ዓይነት የሕይወትም ይሁን የአገልግሎት እርካታ የላቸውም:: ሕይወታቸውና አገልግሎታቸው ጥልቀትና ብስለት የሌለው፥ ያልሰከነና መሬት ያልረገጠ የስሜት ግልቢያ እንዲሆን ያደርገዋል:: ውስብስብ የሆነ ኑሮ ያላቸው መሪዎች ራሳቸውን መግዛት የሚችሉበት አቅምና በራሳቸው ላይ መጨከን የሚችሉበት ድፍረት ስለሌላቸው፤ እንደ ላስቲክ እየተለጠጠ በሚሄዱ የምኞት ዓለም ውስጥ እንዲኖሩ ይገደዳሉ:: ባላቸው ነገር ላይ መርካት ስለማይችሉ ያለ አቅማቸው የሌላቸውን ለማካበት ይወጠራሉ::

2.2 በመጠን የመኖር ዲሲፕሊን በጊዜ ያልተወጣጠረ ኑሮ እንዲኖረን ያደርጋል ማለት ላይሆን ይችላል:: <u>ነገር ግን ከአገልግሎት ብዛት ይልቅ፤ ጥራት ላይ እንድናተኩር ያደርገናል::</u> የውስጣችን እርካታ፥ ምንጩ፥ መነሻው ወይም ምክኒያቱ ውጭ የምናገኘው፥ የምናደረገው፥ ወይንም የምንገዛ ሳይሆን፤ እግዚአብሔር ብቻውን ይሆናል:: ሐዋርያው ጳውሎስ በፊልጵስዩስ 4፥ 10-13 ላይ "...*የምኖርበትን ኑሮ ይበቃኛል ማለትን ትምሬአለሁና:: መዋረድንም አውቃለሁ፥ መብዛትንም አውቃለሁ፤ በያንዳንዱ ነገር በነገርም ሁሉ መጥገብንና መራብንም፥ መብዛትንና መጉደልን ተምሬአልሁ:: ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ::"* እንዳለው ነው::

ሐዋርያው ጴጥሮስም "... *ትጸልዩም ዘንድ በመጠን ኑሩ"* ያለውን መመሪያ ለማስተዋል ስንኖር ኑሮአችን ያልተወሳሰበ ይሆናል:: (1ጴጥ. 4፥7-8) አንዳንድ መሪዎችና አገልጋዮች የተጠሩለትን የእግዚአብሔር ጥሪ ትተው ገንዘብን በመውደድ እንደተጠመዱት ሳይሆን፥ እንደ ጢሞቴዎስ በቅንነት ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ

የሚገደንና የምንጨነቅ እንድንሆን ያደርገናል። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው፡-
*“እንደ እርሱ (ጢሞቴዎስ) ያለ ስለ ኑሮአችሁ በቅንነት የሚጨነቅ ማንም የለኝምና፤ ሁሉ የራሳቸውን ይፈልጋሉና፥ የክርስቶስ ኢየሱስን አይደለም።”*

2.3 በመጠን የመኖር ዲሲፕሊን በውጫዊ የኑሮ ዘይቤ የሚገለጽ የውስጥ ርትዕና ውበት ነው!!! በመጠን መኖር የውስጥና የውጭ መግለጫዎች እውን እንዲሆን ያደርጉታል። የውስጥ ውበት ያለ ውጫዊ መግለጫ (ማለትም በተግባር ያልታየ) ሊሆን አይችልም። በአንፃሩም ውስጣዊ ርትዕና ውበት ሳይኖረው በውጫዊ መግለጫ ብቻ ለመኖር መሞከር የሞተ ሕጋዊነት ውስጥ እንድንኖር ያስገድደናል። ስለዚህ ሁለቱ የአንድ ሳንቲም ገጽታዎች ስለሆኑ በሚዛን ሊጠበቁ ይገባቸዋል።

2.4 በመጠን መኖር (SIMPLICITY)
ከብሕትውና ኑሮ (DUPLICITY) ጋር ሲነጻጸር፡-

እዚህ ላይ መጠቀስ ያለበት ያልተወሳሰበ ኑሮ ከብሕትውና ኑሮ በጣም የሚለይ መሆኑ ነው። <u>አንደኛ</u> ብሕትውና ኑሮ ከ “ብልጽግና ወንጌል” ተቃራኒ የሆነ “የድህነት ወንጌልን” ያስተናግዳል፤ ያልተወሳሰበ ኑሮ ግን ስለ ገንዘብና ንብረት ትክክለኛና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረዳት እንዲኖረን ያደርጋል። የነገር ሁሉ ምንጭ እግዚአብሔር እንደሆነ ስለምናስተውል፥ ከጌታ የተሰጠን ገንዘብ ወይም ንብረት ባለቤቶች ሳንሆን ፤ ባለ አደራዎች እንደሆንን አውቀን በጥንቃቄና በማስተዋል ለክብሩ እና ለሌሎች ጥቅም በደስታ እንጠቀምበታለን። <u>ሁለተኛ</u> የብህትውና ኑሮ ሀብትንና ንብረትን ክዶ ሰውነትን በማጎሳቆል ያምናል፤ ያልተወሳሰበ ኑሮ ግን ጸጋ ከተሞላው እግዚአብሔር የተሰጠ እንደሆነ በማወቅ ንጹሕ በሆነ ደስታ ደስ ይለዋል። የብሕትውና ኑሮ የራስም ሆነ የሌሎችን ኑሮ ለማሻሻል የሚያደርገው ጥረት የለም፤ ያልተወሳሰበ ኑሮ ግን በእጃችን ያለው ገንዘብም ሆነ ንብረት ለራሳችን ጥቅም የተሰጠ የሚታቆር ሳይሆን፤ ለሌሎች ሰዎች እያካፈልን በሕይወታቸው ለውጥ እንዲመጣ ለማድረግ እንደሆነ ያምናል።

**2.5 በመጠን መኖር በውጭ ሲገለፅ:-**

አዙሳ ፓስፊክ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ አስተማሪ የሆነው ሪቻርድ ፎስተር "ቀላል ኑሮ" (SIMPLICITY) ውጫዊ መግለጫ መለኪያዎች የሚሆኑ አሥር ነጥቦች አቅርቧል::[67]

2.5.1 "ምንም ዓይነት ነገር ብትገዙ የኑሮአችሁ ዓይነት እንዲገልፅ ሳይሆን÷ ለቤታችሁ ያለውን ጠቀሜታ በማየት ይሁን::

2.5.2 በእናንተ ላይ የተለየ ልማድ ወይም ሱስ ከሚያመጣ ነገር ራሳችሁን ጠብቁ:: (ለምሳሌ:- ቡና÷ ሻይ÷ ለስላሳ÷ ቲቪ÷ ኢንተርኔት÷ ሶሻል ሚድያ÷ወዘተ.)

2.5.3 ያላችሁን ነገር ለሌሎች ሰዎች ማካፈልም ይሁን መስጠት ባሕሪያችሁ ይሁን::

2.5.4 ዘመናዊ ጋጀቶች ለመግዛትና ለማካበት ከመጓጓት÷ ያላገኛችሁት እንደ ሆን ዓለም እንደሚገለበጥ ከማሰብ ራሳችሁን ጠብቁ:: አዲስ ሞዴል ሳይገዛም ኖረን እናውቃለን::

2.5.5 ባሉን ነገሮች ከራሳችን ጋር ሳናጣብቅ ደስ ብሎን መጠቀም መቻል አለብን::

2.5.6 እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥረት አይታችሁ መደነቅ÷ የጌታን አስደናቂ ሥራን ማመስገን÷ እና ከጊዜ ወደ ጊዜ ከከተማ በመውጣት የእጆቹን ሥራ እያዩ ለፍጥረታት ውበት የሰጠውን መንፈስ ቅዱስን ማክበር ልማዳችሁ ይሁን:: (መዝ. 24÷1÷ 104÷30÷ 139÷14)

2.5.7 በብድር (በተለይም ወለድ ባለው ብድር) ነገሮችን በመግዛትና ከሚያስፈልገን በላይ በመሰብሰብ የሌሎች መጠቀሚያ ከመሆን ራስን መግዛት መለማመድ አለባችሁ::

2.5.8 በሰዎች ፊት አጉል ሙገሣ ስለ ሰው ከመናገርና÷ ግማሽ እውነት ከመናገር መቆጠብ የዘወትር ባሕርያችሁ ይሁን:: የማታደርጉትን ነገር ለሰዎች ቃል ከመግባትና ግምታዊ ንግግር ከመናገር ራሳችሁን ተቆጣጠሩ::(ማቴ. 5÷37፤ ኤፌ. 4÷25)

2.5.9 በሌሎች ሰዎች ላይ ጫና ከሚያመጣ÷ ራሳቸውን የበታች አድርገው እሚያዩ ከሚያደርግና÷ ከሚጨቁን መንገድ እና አሠራር ሰዎች የእኛ የስልጣንና

---

[67] Richard J. Foster, *Celebration of Discipline - The Path to Spiritual Growth*, (New York: Harper & Row Publishers, 1978).

የኃይል እርከን መወጣጫ መሰላል ወይም መጠቀሚያ አድርጎ ከመውሰድ ራሳችሁን ማንፃት ይኖርባችኋል።

2.5.10 'በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን ከመፈለግ' ከሚያግዳችሁ ማናቸውም ነገር መራቅ የዘወትር መመሪያችሁ ይሁን።"[68]

### 3. በእግዚአብሔር የመደገፍ ዲሲፕልን፡-
### (THE DISCIPLINE OF DEPENDENCY)

በእግዚአብሔር የመደገፍ ዲሲፕልን ያለ እርሱ ምንም ነገር ማድረግ እንደማይቻለን በማወቅና በጥድፊያ ለሚደረግ ሰበዓዊ ጥበብ የተጋለጥን መሆናችንን በመቀበል፣ በየዕለቱ የቃሉን ድምፅ እየሰማን በጸሎት መንፈስ ለአመራሩ ምላሽ መስጠት ነው። (መዝ. 25፥4-5፥ 14፣ 119፥11፥105) ይህ ዲሲፕልን በየቀኑ የእግዚአብሔርን ፊት እንድንፈልግ፥ ፍለጋውንም እንድንከተል፥ የሐሳብ ሂደታችንንም ሳይቀር እየቀደሰን እንዲመራን ልባችንን ለመክፈትና ሕይወታችንም ጌታ ኢየሱስን እየመሰለ እንዲኖር በፍፁም ፍርሃትና መንቀጥቀጥ ለመኖር ያስችለናል።

በእግዚአብሔር የመደገፍ ዲሲፕልን በውስጣችን እያደገ መምጣቱ በተለያዩ መንገዶች ልንለካው እንችላለን። <u>አንደኛ</u> ለእግዚአብሔር ቃል ያለን አክብሮትና በሕይወታችንም የምንሰጠው ቦታ ምን ያህል መሆኑን በማየት ነው። በየቀኑ የጌታን ቃል ለማጥናት የሚኖረን የተከፈተ ልብ፥ ከፊደላት ማንበብ ያለፈ ሕያው ቃል የሆነና የቃሉ እንብርት የሆነውን ጌታ ኢየሱስን ለማየትና ከእርሱም ጋር ልዩ ህብረት ማድረግ መቻላችን ድምፁንም ከቃሉ መስማታችን ለተናገረን ቃል በሙሉ ፈቃደኝነት መታዘዛችን (የሐዋ. ሥራ 17፥10-11) የተማርነውንም ለሌሎች ሰዎች ማካፈላችን ይህንን ዲሲፕልን እያሳደግን መምጣታችን ምልክት ነው።

<u>ሁለተኛ</u> ለመንፈስ ቅዱስ አመራር ያለን መስጠት፥ መደገፍና ግንኙነት በጣም ወሳኝ ነው። በራስ የአእምሮ ጥበብ፥ በዓመታት ልምምድ፥ በአካዳሚክ እውቀት፥ ወይንም እንዲሁ በመሰለኝ (በነሲብ) ከመደገፍ ይልቅ፣ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መደገፍ እግዚአብሔርን በቁም ነገር መውሰዳችንን ያሳያል። <u>ሦስተኛ</u> እግዚአብሔር የሕይወት ምንጭና ባለቤት መሆኑን በማወቅና በማመን፥ በክንዱ ሊደግፈን በማዳኑም ሊታደገን፥ በቸርነቱ ሊያጠግበን፥ በተአምራቱ ሊያስደንቀን፥ ከጅማሬአችን ይልቅ ፍፃሜአችን የበለጠ ሊያደምቅና ሊያሳምር እንዳለው በመታመን፥ በእርሱ

---

[68] Ibid., 78-83.

ጅትና ብርቱ ክንድ ተደግፈን መውጣትና መግባታችን በልባችን ለእግዚአብሔር የሰጠነውን ትልቅ ሥፍራ ያሳያል።

4. የወጥነት ዲሲፕልን–

(THE DISCIPLINE OF INTEGRITY)

የወጥነት ዲሲፕልን ማንም ሰው በማያየን ሥፍራም ሳይቀር ትክክለኛና እውነት የሆነውን ነገር ለማድረግ መቻል ነው!!! ተመልካች/ ታዛቢ ኖረ አልኖረ፤ የሚያውቀን ሰው ኖረ አልኖረ፤ ጽድቅና እውነት የሆነውና ጌታን የሚያስከብረውን ነገር ለማድረግ የየዕለቱ ዲሲፕልን እንዲሆን ማድረግ ነው። ወጥነት ለራሴ እውነት መናገር ሲሆን፥ ሐቀኝነት ደግሞ ለሌሎች ሰዎች እውነትን የመናገር ዲሲፕልን ነው። ሌሎችን ለማሳመንና ለመማረክ የምንታመን መሆን አለብን፤ የታመነ ሰው ለመሆን ደግሞ የሕይወቱን ንጽሕና የጠበቀ ሰው መሆን ይኖርብናል። የሕይወትን ንጽሕና ለመጠበቅ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ንጹሕ ሕሊናና ታማኝነትን ይጠይቃል። (የሐዋ. ሥራ 24፥16፤ ሮሜ 11፥14፤ 2ቆሮ. 6፥3፥ 8፥20-21)

- የወጥነት ዲሲፕልን ያለው ሰው በተቃውሞና ተቃራኒ የሆነ የዋጋ አሰጣጥ መሃል ጽናትና ብርታትን ያሳያል። ከስህተት አሠራር ይልቅ እውነተኛ የሆነውን፤ ከምግባረ ብልሹነት ይልቅ ለጊዜያዊ ጥቅም ከማጎብደድ ይልቅ፥ የሥነ ምግባር መለኪያ መጠበቅን፤ ከታዋቂነት ይልቅ እውነትን፤ ከስኬታማነት ይልቅ ታማኝነትን ይመርጣል። እነዚህ ጉዳዮች አንድ መሪ ወጥነት ያለው መሆኑ መግለጫዎች ናቸው።
- የሰው የተስፋ ቃሎች በሥራ ተተርጉመው እስከሚታዩ ድረስ ቃላት ብቻ ያውም ሥጋ ያልለበሱ ቃላት ብቻ ናቸው ። የመሪዎች ቃል የሚከበረው በጠጠረ እውነታ ውስጥ ባሕርያቸው ተፈትኖ ሲወጣ ብቻ ነው። ስለዚህ መሪዎች ወጥነት ያለ ዲሲፕልን ለመኖር ይህንን ቢጠብቁ በየዘመናቱ ቃላቸውን የሚመዝን፥ ክቡርና ክብደት ያለው፥ ሰዎች ለመስማት የሚጓጉት፥ የታመነና የማይቀየጥ እውነት እየሆነ ይመጣል!!!
- ወጥነት ያለው ሰው :-

✓ በልቡ የሚያስበውን ይናገራል፤ በአፉ የሚናገረውንም በልቡ ያስባል። (መዝ. 19፥ 16፤ ኤፌ 4፥15፥25፥29)፤

✓ አባይ ሚዛን የለውም (ምሳሌ 20፥10፥11፥1፥20፥17)፤ ሰዎችንም በአድልዎ አይይዝም፥ አይመለከትም (ያዕቆብ 2፥1-13)

✓ የተናገረውን ቃል ይጠብቃል (መዝ. 15፥4)

✓ የሕይወትና የአገልግሎት መመሪያ ያለው ሰው ነው:: ምንም ያህል ዋጋ ቢያስከ ፍለውም እውነት ለሆነ ነገር ይቆማል:: እውነትን ለመሸራረፍ፥ ለመቀያየጥ፥ ለማመቻመች፥ ወይንም ለመሸፈን አይሞክርም:: ለእውነትና ለጽድቅ ከሆነ፥ ከዚያ ላነሰ ነገር "እምቢ" ማለት የሚችል አቅም አለው::

## 5. የጥሞና ዲሲፕልን:-

## (THE DISCIPLINE OF SOLITUDE)

የጥሞና ዲሲፕልን ሕይወታችን በእግዚአብሔር እና በእግዚአብሔር ሐሳብ እን ዲዋጥ ለማድረግ፥ ለተወሰነ ጊዜ ከማንም ሰው ጋር ሳንገናኝ ለብቻችን በጌታ ፊት የመሆን ዲሲፕልን ነው:: ይህ ጊዜ ስለ አገልግሎታችን የምናስብበት ወይንም የምና ቅድበት ጊዜ ሳይሆን፤ የእግዚአብሔርን ፊት የምናይበት፥ በሐሳቡ ውስጥ የምንዋጥ በት፥ ከማንምና ከምንም ነገር በላይ ሉዓላዊነቱን የምንገልጽበት ልዩ የመሰጠት ጊዜ ነው:: ይህንን ለማድረግ ጊዜና ቦታ መወሰን ይኖርብናል:: (ማቴ. 6፥6፤ ማር. 1፥35 ፤ ሊቃስ 4፥42-44፤ ማቴ. 14፥23፤ ሉቃስ 5፥16፤ ዮሐ. 8፥1)

የጥሞና ዲሲፕልን የውስጥ ጸጥታና የልብ እርጋታ ነው:: ይህ ዓይነት የልብ እርጋታ በሰዎች መካከል መሆን አለመሆናችን አያግደውም:: ውስጣዊ መረጋጋት ካለ በውጫዊ ነገሮችም ይከሰታል:: ለብቻችን በእግዚአብሔር ፊት በጥሞና ለመሆን የሚያስፈልገን ከሰዎች ለመራቅ ወይም ለመለየት ስለፈለግን ሳይሆን፤ ይልቁንም በሰከነና በነጠረ አገልግሎት እነሱን ለማገልገል የበለጠ እንድንሠራና እንድንዘጋጅ ስለሚያደርገን ነው!!! (ማቴ. 4፥1-11፥14፥13፥23፥ 17፥1-9፥26፥36-46) የጥሞና ዲሲፕልን ሳይኖረን መንፈሳዊነት ያለው ሕይወት ለመኖር አንችልም::

እዚህ ላይ ልንጠቅሰው የሚገባን አንድ እውነት አለ:: ይኸውም የጥሞና ዲሲፕ ልን ከእግዚአብሔር ሕዝብም ጋር ካለን ሕብረትና የግንኙነት ሥምረት ጋር ሚዛና ዊ በሆነ መንገድ ሊያዝ ይገባዋል:: ምክኒያቱም አንድ መሪ ከሕዝቡ ጋር መደባለቅን እየወደደ፥ የጥሞና ጊዜ ለብቻው በእግዚአብሔር ፊት ለመሆን ካልቻለ ብስለት የሌ ለው፥ ስሜታዊና ግልብ የሆነ አገልጋይ ይሆናል:: በአንፃሩም የጥሞና ዲሲፕልን ኖሮት ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ሕብረት ማድረግ የማይችልና ሕዝቡ ከመድረክ ስብከቱ ሌላ እንዲያውቁትና እንዲቀርቡት የማይፈልግ ከሆነ፥ የማንንም ሰው ሕይ

ቶት የማይነካ፥ በሌሎች ላይ ሕይወትን ሊዘራ የማይችልና፥ የተነጠለ መንፈስ ያለው ሰው ይሆናል።

በጥንት ዘመን ከኖሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች መካከል ፍራንሲስ ኦፍ አሲሲ (FRANCIS OF ASSISI = 1182 - 1226 A.D.) ልዩ የጥሞና ዲሲፕልን የነበረው ስለሆነ የሚከተለውን ሐሳቡን በጽሁፉ አስፍሯል፦

◆ "ጌታ ሆይ፥ የሰላም መሣሪያ አድርገኝ፦

- ጥላቻ ባለበት፥ ፍቅርን ለመዝራት፤
- መጎዳት ባለበት፥ ምህረትና ይቅርታን ለመግለፅ፤
- ጥርጣሬ ባለበር፥ እምነትን ለማሳየት፤
- ተስፋ መቁረጥ ባለበት፥ ተስፋን ለመስጠት፤
- ጨለማ በሰፈነበት፥ ብርሃንን ለማሳየት፤
- ሐዘን ባለበት፥ ደስታን ለማሰራጨት።

ኦ! መለኮታዊ አምላክ ሆይ፦

- የራሴን ምቾት ከመፈለግ ይልቅ፥ የሌሎችን ምቾት ለመጠበቅ፤
- ሌሎች እኔን እንዲረዱኝ ከመፈለግ ይልቅ፥ ሌሎችን ለመረዳት እንድችል፤
- በሌሎች ለመወደድ ከመፈለግ ይልቅ፥ ሌሎችን ለመውደድ እንድችል በጸጋህ አስችለኝ ።

ምክኒያቱም፦

- በመስጠት ነው፥ የምናገኘው፤
- ሌሎችን በምህረት በመቀበል ነው፥ ይቅርታን የምንቀበለው፤
- በመሞት ነው፥ የዘላለምን ሕይወት የምናገኘው።"[69]

◆ ሲ ኤስ ሉዊስ የሚባለው ክርስትያን ፈላስፋ የነበረው ደግሞ እንዲህ ብሏል፦
"ሰነፎችና ሃኬተኞች ብቻ ናቸው የሚባክኑት።"[70]

---

[69] www.catholic-forum/Saints/pray0027.htm. (accessed July 20, 2013). See also www.wikipedia.org/wiki/prayer-of-Saint-Francis. (accessed July 20, 2013)
[70] Walking with Yeshua.blogspot.com/2007/06/one-to-consider.html. (accessed July 20, 2013)

❖ የጥሞና ዲሲፕልን እንዲኖረን ካስፈለገ የሚከተሉትን ነገሮች ማሰቡ በጣም ይረዳል፥

➢ ከቤታችን ውጭ ፓርክ፥ ጫካ፥ ወንዝ፥ ሀይቅ ወይንም ባህር ዳር፥ወዘተ. ፈልጎ ለብቻችን የምንሆንበትን ጊዜ መወሰን፤

➢ ከአፋችን የሚወጣውን የቃላት ብዛት የተመጠነ እንዲሆን ራስን መቆጣጠር፤ የጥቂት ቃላት ሰው መሆን፤

➢ ንግግራችንን ቀጥተኛ፥ ሐቀኛና ግልፅ እንዲሆን በማስተዋል መናገር፤

➢ የምንናገረውን የምናደርግ፤ ያደረግነውን የምንናገር ሰው መሆን፤ የገባነውን ቃል መፈፀም፤

➢ ለአንድ ቀን ሙሉ (ለሃያ አራት ሰዓት) ቢቻል በየሦስት ወሩ ምንም ዓይነት ቃል ከአፋችን ሳናወጣ በዝምታ ለመቆየት መቻል፤

➢ በዓመት ውስጥ ለአራት ጊዜ ያህል ከሦስት ሰዓት ላላነሰ የሕይወታችንን ዓላማ ለማስተካከልና ለመገምገም ጊዜ መውሰድ።

**6. የዝምታ ዲሲፕልን፡-**

**(THE DISCIPLINE OF SILENCE)**

የዝምታ ዲሲፕልን ከጫጫታና ከውካታ መለየት፥ የተለያዩ ዕረፍት የሚነሱን ድምፆችን ማጥፋት፥ (ለምሳሌ፡- ቲቪ፥ ሬድዮ፥ ሙዚቃ፥ ኢንተርኔት፥ ስልክ፥ ሞባይል፥ ወዘተ.) የተሰበሰበና የሰከነ ሰው ሆኖ ፀጥታን ሳይፈሩ ተዘልሎ መቀመጥ፤ የወፎችንና የውሃን ድምፅ እየሰሙ በጫካ መሃል መጓዝ፤ በሰዎች መሃል ስንሆን ደግሞ የጥቂት ቃላት ሰው መሆንን ያመለክታል።

❖ <u>በአመራራችን በስብሰባ ላይ በምንሆንበት ጊዜም ሁልጊዜ እኛ ብቻ መናገር አይኖርብንም። የዝምታ ዲሲፕልን ምላሳችንን በጥርሳችን መካከል እንድን ነክስ፥ የሌሎችን ሰዎች ሐሳብ ቀጥለን የምንናገረውን እያሰብን ሳይሆን፥ በረጋና በተሰበሰበ መንፈስ እንድናደምጥ፥ በዙሪያችን ያለውን ዓለምም ይሁን፥ የራሳችንን ገፅታ (SELF IMAGE) ለመቆጣጠር ከመሞከር ተቆጥበን ልበ ሰፊ ሰው እንድንሆን ያደርገናል።</u>

❖ በቃላችን ብዛት የሌሎችን ስዎች አዕምሮ ለመያዝና ለመማረክ፥ እንዳይረሱ ንና ይልቁንም በየጊዜው እንዲያስቡን ለማድረግ ሰዎችን ከማታለል እንድን ቆጠብ ያደርገናል። ብዙ መናገር ስናበዛ የምንናገረው ነገር ከሆነው ነገር

ጋር ስለማይጣጣምና አብዛኛውን ጊዜ ተቃራኒ ስለሚሆን የጥቂት ቃላት ሰው ልንሆን ይገባናል።

- የዝምታ ዲሲፕልን ከአመራራችን ጋር በተያያዘ በሚኖሩን ስብሰባዎች መሃ ልም እኛ የመጨረሻውን ቃል መናገር አይኖርብንም። የብዙ መሪዎች ሕይ ወት የተቦረቦረውና አብረውን የሚያገለግሉ ሰዎች ጸጋ እያቀጨጨ የመጣ ው የመጨረሻውን ቃል እኛ ካልተናገርን ነገር ሁሉ የሚበተን መስሎን ስለምንታገል ነው።
- የዝምታ ዲሲፕልን መሪዎች የተቀመመና ጸጋ የሞላበት፥ በሌሎችም ሕይ ወት ፀጋን የሚጨምር፣ የሰከነ፥ የነጠረና የበሰለ ቃላት ከአፋቸው እንዲወጣ ያደርጋል። ብዙ መናገር የሚያበዙ መሪዎች ግን ኤዕምሮአቸው ባዶ እየሆነ ስለሚሄድ ንግግራቸውም የቀጠነ፥ ለዛ የሌለው፥ ራስን ማዕከል ያደረገና ማንንም ሰው የማያንጽ እየሆነ ይመጣል።

7. የጾም ዲሲፕልን፦

(THE DISCIPLINE OF FASTING)

የጾም ዲሲፕልን በእግዚአብሔር ቃል በብዛት የተጠቀሰ ከመሆኑም ሌላ፣ ጸሎ ታችን የትኩረት አቅጣጫ ያለውና የእግዚአብሔርን ፊት ያለ ምንም ግርዶሽ እንድ ናይ እጅግ የሚረዳን አስፈላጊ ነገር ነው። የፆም ዲሲፕልን ከምግብና ከሚጠጣ ነገር (ማለትም፦ ከቡና፥ ከሻይ፥ ከለስላሳ መጠጥ) ተለይተን ውሃ በመጠጣት ብቻ ለተወ ሰኑ ቀናት በእግዚአብሔር ፊት በፀሎት መቆየትን ያመለክታል። ከየትኛዎቹም መንፈሳዊ ዲሲፕልኖች ይልቅ፣ የፆም ዲሲፕልን የትኛው ነገር እንደገዛን የሚገልጥ መለኪያ ነው።

- የጾም ዲሲፕልን ከሚታየው ዓለም የተሻለና የበለጠ የማይታይና ዘላለማዊ ዓለ ም እንዳለ የሚያስረግጥልን ነው። (ዘጸ. 8፥1-6፣ ማቴ. 4፥1-11፣ ዮሐ. 4፥32)
- የጾም ዲሲፕልን ምንም እንኳን ከሚበላና ከሚጠጣ ነገር ተቆጥበን የምናደርገ ቢሆንም፣ ታይቶ የማይጠገብ የእግዚአብሔርን ፊት በጥልቀት የምናይበት፥ ፈ ቃዱንም የምናስተውልበት ጊዜ ነው። (መዝ. 35፥13፣ 2ዜና መዋዕል 7፥14፣ ዕ ዝራ 8፥ 21-23)
- የጾም ዲሲፕልን በሌላ መንገድ ሊመጣ የማይችል አስደናቂ ድንቅና ተአምራት እንዲመጣና ተራራው እንዲደረመስ፥ አዋጅ በአዋጅ እንዲሻር፥ ጨለማው እን

ዲገፈፍ፥ በግለሰብ፥ በቤተ ሰብ፥ ወይንም በሕዝብ ልብ ውስጥ እፎይታ እንዲ መጣ የማድረግ ኃይል አለው!!! (2ዜና መዋዕል 7፥14፤ ዕዝራ 8፥21-23፤ አስቴር 4፥13-17፤ የሐዋ. ሥራ 13፥1-3)

## 8. የቅድስና ወይም የንጽሕና ዲሲፕልን፡-

**(THE DISCIPLINE OF CHASTITY)**

የቅድስና/ የንጽሕና ዲሲፕልን ከማናቸውም ዓይነት ከትዳር ውጭ የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት፥ ንጽሕና ከሌለው አስተሳሰብ፥ ወይንም ቅድስና ከሌለው ምኞት ራስን በመቆጣጠር የሕይወትን ቅድስና/ ንጽሕና መጠበቅ የመቻል ዲሲፕል ን ነው:: (ማቴ. 5፥27-28፤ 19፥3-12፤ 1ተሰ. 4፥1-7፤ ኤፌ. 5፥3-14)

- ❖ በአመራር ላይ የተቀመጡ መሪዎችና አገልጋዮች የሕይወታቸውን ቅድስናና ንጽሕና ለመጠበቅ እንደ ኢዮብ ከአይናቸው ጋር ቃል ኪዳን በመግባት ንጽሕናና ቅድስና የሌለውን ነገር ከማየትም ይሁን ከማሰብ ራሳቸውን ሊገዙና ሊቆጣጠሩ ይገባቸዋል:: (ኢዮብ 31፥ 1-15፤ 2ጢሞ. 2፥22)
    - ❖ የኃጢአት ፈተና አብዛኛውን ጊዜ ራሱን እያስታወቀ ነው የሚመጣው:: በጣም የሚገርመው ግን ብዙ ሰዎች ፈተናው ይጥማቸዋል::
    - ❖ ከዝሙት ፈተና ለመጠበቅ ከተፈለገ አማራጭ የሌለው መፍትሔው በቃል ኪዳን ከተሣሠርናት ሚስት (ባል) ጋር ቅንነት ባለው መንገድ የጠለቀ ፍቅር ና ጓደኝነት በየዘመናቱ ማጸበርና ማሳደግ ነው::
    - ❖ ምክር የመስጠት አገልግሎት (በተለይም ተቃራኒ ጾታ ጋር) በሚደረግበት ጊዜ መሪዎች ሊያደርጓቸው የሚገቡ ጥንቃቄዎች የሚከተሉት ናቸው:-
- ➢ አንደኛ የምክር አገልግሎት በምንሰጥበት ጊዜ ሦስተኛ ሰው አብሮ ከሌለ በስተቀር ከተቃራኒ ጾታ ጋር ላለማድረግ መወሰን:: በተቻለ መጠን ሦስተኛው ሰው ሚስታች ን ወይም ባላችን ቢሆን ይመረጣል::
- ➢ ሁለተኛ የምክር መስጠት አገልግሎት በስልክ ለመጨረስ መቻል ነው::
- ➢ ሦስተኛው በቤተ ክርስቲያን ግቢ ካልሆነ በስተቀር ሌላ ቦታ፤ የተቃራኒ ጾታው ቤት ፥ ወይንም ምግብ ቤት፥ ወይንም ሆቴል እንዳይሆን በጥብቅ መወሰንና መታገድ::